# አዲስ ዘመን

እናድ

ማክሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 218 ሚያዝያ 8 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# ከቱሉ ቦሎ እስከ ኬላ የሚወስደው መንገድ 95 በመቶ ተጠናቀቀ

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- ከቱሉ ቦሎ እስከ ኬላ 80 ኪሎ ሜትር የሚሸፍነው የመንገድ ግንባታ 95 በመቶ መጠናቀቁን የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር አስታወቀ።

በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ቡታ ጅራ አካባቢ ኮንስትራክሽን ጽሕፈት ቤት ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ገዛኸኝ ወከለ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳሉት፤ ፕሮጀክቱ አንድ ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር በጀት ተይዞለት በ2010 ዓ.ም ግንባታው የጀመረ ሲሆን በአሁኑ ወቅትም ጠቅላላ ግንባታው ከሚሸፍነው ሰማንያ ኪሎ ሜትር ውስጥ ሰባ አምስት ኪሎ ሜትር ወይም 95 በመቶ ተጠናቋል ብለዋል።

ይህ ፕሮጀክት መነሻውን ቱሉ ቦሎ ከተማ ላይ በማድረግ ሦስት ወረዳዎችን የሚያቋርጥ ሲሆን፤ በስፍራው የሚገኙትን አጎራባች ከተሞች ከአዲስ አበባ ቡታጅራ ሆሳዕና፣ ከአዲስ አበባ ወልቂጤ ጅማ መስመር

ከቱሉ ቦሎ እስከ ኬላ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








**"ኢትዮጵያ በቀጣናው የውሃ ሀብትን በፍትሐዊነት መጠቀም እንዲቻል ሰፊ ተግባራት እያከናወነች ነው"**

- ኢንጂነር ጌድዮን አስፋው
የዓባይ ግድብ ቴክኒካል ቡድን ተደራዳሪ

ገጽ 4



አቶ በያን ተሰማ

# አረንጓዴው ሰው

**ተስፋ ፈሩ**

አቶ በያን ተሰማ የድሬዳዋ ከተማ ነዋሪ ናቸው። ሰው ሲተዋወቁ ከስማቸው በኋላ "ወይም" ብለው በኩራት የሚያስከትሉት የአደባባይ ስም አላቸው። ከስማቸው አብልጠው የሚወዱት ይህ መጠሪያ "አረንጓዴው ሰው" ይሰኛል።

አረንጓዴው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# በአማራ ክልል ከ385 ሺህ ኩንታል በላይ የበጋ ስንዴ ተሰብስቧል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በዘንድሮ የበልግ ወቅት ከ385 ሺህ ኩንታል በላይ የበጋ ስንዴ ምርት መሰብሰቡን የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ።

በክልሉ የግብርና ቢሮ የመስኖ አትክልትና ፍራፍሬ ባለሙያ አቶ ተሻለ አይናለም ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በአማራ ክልል ከ151 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በበጋ መስኖ ስንዴ ለምቷል። በዚህም ከዘጠኝ ነጥብ አራት ሚሊዮን በላይ ኩንታል ምርት ይጠበቃል።

በክልሉ ደጋማና ቆላማ አካባቢዎች የደረሰውን ሰብል የመሰብሰብ ሥራ ተጀምሯል ያሉት አቶ ተሻለ፤ 38 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የለማው ስንዴ ተሰብስቧል፡፡ በአጠቃላይ እስከ አሁን ከ385 ሺህ ኩንታል በላይ ምርት ከበጋ መስኖ ስንዴ ማግኘት ተችሏል ብለዋል።

አርሶ አደሩ የበጋ መስኖ ስንዴ ውጤታማነትን ተገንዝቦ በንቃት እየተሳተፈ ይገኛል ያሉት አቶ ተሻለ፤ ለአርሶ አደሩ የማዳበሪያ፣ ምርጥ ዘር፣ የውሃ ፓምፕ፣

በአማራ ክልል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






# ያለ ጊዜ መውለድን ለመከላከል የቅድመ ወሊድ ክትትልን ማጠናከር ይገባል

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

አዲስ አበባ፡- ያለ ጊዜ መውለድን ለመከላከል የቅድመ ወሊድ ክትትል ማጠናከር ይገባል ሲሉ በየካቲት 12 ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ፣ የአበበች ጎበና የእናቶችና ሕፃናት ሆስፒታል በሕፃናትና ልጆች ሕክምና ክፍል ረዳት ፕሮፌሰር ዜናዊት አለማየሁ ተናገሩ፡፡

በሆስፒታሉ ሙቀት ክፍል ከሚገቡ 100 ጨቅላ ሕፃናት መካከል በአማካይ ከ30 እስከ 50 የሚሆኑት ያለ ጊዜያቸው የተወለዱ ናቸውም ብለዋል፡፡

የጨቅላ ሕፃናት ያለ ጊዜ መለወድ በርካታ ምክንያቶች እንዳሉት የተናገሩት ረ/ፕሮፌሰር ዜናዊት፤ ከእርግዝና በፊት የነበረና በሚገባ ያልታከመ ግፊት፣ በእናቲቱ ላይ ያሉ እንደ ልብ፣ ኩላሊትና ሌሎች ሕመሞችም ያለጊዜ መውለድን እንደሚያስከትሉ ዘርዝረዋል፡፡

በእናቲቱ ላይ የቆየ የደም ማነስም ለጨቅላ ሕፃናት ያለ ጊዜ መወለድ ምክንያት መሆኑንም ረ/ፕሮፌሰር ዜናዊት አንስተዋል፡፡

እንደ እርሳቸው ማብራሪያ፣ በተለምዶ ሾተላይ የሚባለው ችግርና በእናት ማህጸን ላይ የሚፈጠሩ ወይም ከማህጸን ከአፈጣጠር ጋር የተያያዙ ችግሮችም እንዲሁ ያለ ጊዜ መውለድን እያስከተሉ ካሉ ሰበቦች መካከል ይጠቀሳሉ፡፡

በማህጸን አካባቢ የሚፈጠር ኢንፌክሽንም የእንሽርት ውሃ ያለ ጊዜው እንዲፈስ በማድረግ ያለ ጊዜው መውለድን ያስከትላል፡፡

የንጥረ ነገር እጥረት ያለባት እናትም ለልጇ ያለ ጊዜ መወለድ ምክንያት ልትሆን ትችላለች፡፡

በሕፃናቱ ላይ ከአፈጣጠር ጋር የተያያዙ ችግሮች በሚኖሩበት ጊዜና ሁለትና ከዚያ በላይ መንታ ጽንስ በሚፈጠርበት ጊዜም ከአቅም በላይ የማህጸን መወጠርን ስለሚያመጣ ምጥ ያለጊዜው እንዲመጣ ምክንያት ሊሆን እንደሚችልም ፕሮፌሰሯ አብራርተዋል፡፡

ካለጊዜያቸው የተወለዱ ጨቅላ ሕፃናት ላይ ወዲያው የሚከሰቱና እያደጉ ሲመጡ የሚከሰቱ የጤና ችግሮች ሊኖሩ እንደሚችሉ ረዳት ፕሮፌሰሯ ያስረዳሉ፡፡

በአእምሮ እድገት፣ ልብ፣ ኩላሊት፣ የመተንፈሻ አካልና አንጀት ላይ የሚከሰቱ ችግሮች ከጨቅላ ሕፃናት ያለጊዜ መወለድ ሳቢያ ከሚከሰቱ መካከል በዋናነት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ሕፃናቱ የጽንስ ጊዜያቸውን የጨረሱ ባለመሆናቸውና አንጀታቸውም ያልዳበረ በመሆኑ በጊዜ መመገብ ያለመቻል ችግር ይገጥማቸዋል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞም ለአንጀት ቁስለት፣ ለስኳር መውረድና ለደም ግፊት ይጋለጣሉ፡፡

እያደጉ በሚመጡበት ጊዜም በትምህርት አቀባበላቸው ላይ ከሌሎች ልጆች በተለየ የመዘግየት ሁኔታ የሚስተዋልባቸው ይሆናሉ፡፡

የጨቅላ ሕፃናት ያለ ጊዜ መወለድ በእናቲቱም ሆነ በሕፃኑ ላይ ከሚያስከትለው የጤና ችግር በተጨማሪ እናትና ልጅ በሆስፒታል እንዲቆዩ ስለሚገደዱ የሥነ ልቡና ችግር ያስከትላል፡፡

እናቶች ከወለዱና የሆስፒታል ጊዜያቸውን ከጨረሱ በኋላ ልጆቻቸው በሆስፒታሉ የሚቆዩ ከሆነ ለእናቲቱ ምቹ የማደሪያ ስፍራ የተመቻቸ ቦታ ስለማይኖራቸው ለመጉላላት እንደሚዳረጉም ነው ፕሮፌሰር ዜናዊት የሚናገሩት፡፡

ልጃቸውን በጊዜ የጡት ወተት መስጠት አለመቻላቸውም በእናትና ልጅ መካከል ሊኖር የሚገባው ቅርርብ ማግኘት ባለመቻላቸው ለድባቴና ሌሎች ሥነ ልቡናዊ ችግሮችም የመጋለጥ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

እንዲህ ያሉ የጤና ችግሮችን ከእናትና ልጅ ላይ ለመከላከል የጤና ተቋማትና ባለሙያዎች አንደኛ ቅድመ እርግዝና ምርመራና አንዲት ሴት ነብሰ ጡር ከሆነች በኋላም ቅድመ ወሊድ ክትትልን በአግባቡ እንድትከታተል የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ እንዲሠሩ አሳስበዋል፡፡



ረዳት ፕሮፌሰር ዜናዊት አለማየሁ

ያለጊዜ የመውለድ ችግርን ሙሉ በሙሉ ማስቀረት ባይቻል እናቶች በእርግዝናቸው ወቅት በሚያደርጉት ክትትል ግን በከፍተኛ መጠን መቀነስ እንደሚቻል የተናገሩት ፕሮፌሰር ዜናዊት፤ እናቶች ከእርግዝና በፊትም ሆነ ከእርግዝና በኋላ ወደ ጤና ተቋም በመሄድ ምርመራና ክትትል እንዲያደርጉ መክረዋል፡፡



# መመሪያው ጾታዊ ጥቃትን ለመከላከልና ወጥ የሆነ አሠራር ለመዘርጋት ያግዛል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- መመሪያው ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃትን ለመከላከል ፣ የምላሽ አሰጣጥ ውጤታማነትን ለማሳደግ እና ወጥ የሆነ አሠራርን ለመዘርጋት እንደሚያስችል የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከዩ ኤን ኤፍ ፒ ኤ ጋር በመተባበር ብሔራዊ የሥርዓተ ፆታ መከላከልና ምላሽ መስጠት የአሠራር መመሪያን በትናንትናው እለት ሥራ ላይ አውሏል።

በወቅቱ የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ፍሬህይወት አበበ እንደገለጹት፤ ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃትን የመከላከል ተግባር የአንድ ተቋም ብቻ ሳይሆን በቅንጅት የሚሠራ ሥራ ነው።

በዋናነትም ጥቃቱ እንዳይፈጸም የመከላከል እና ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ ትኩረት ተሰጥቶት እንደሚሠራ የገለጹት ሚኒስትር ዲኤታዋ፤ እንደ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤትም የአምስት ዓመት እቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው ብለዋል።

ጾታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶችን ከመከላከል አንጻር ብዙ እንቅስቃሴዎች ቢደረጉም ወጥ የሆነ ሰነድ ባለመኖሩ ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚሠሩ ሥራዎች ወጥ ያልሆኑና አግባብ የሌላቸው መሆናቸውን ተናግረዋል።

ይህ መመሪያ ይበልጥ ጾታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች ፈጣን ምላሽ እንዲያገኙ የሚያደርግ እና ተቋማቱ የሚሠሯቸውን ሥራዎችም ውጤታማ የሚያደርግ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር በሚኒስትር ዴኤታ ማዕረግ አማካሪ የሆኑት አቶ ጌታቸው በዳኔ በበኩላቸው፤ በተዛባ የሥርዓተ ጾታ አመለካከት፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እኩልነት መጓደልና በሌሎች አባባሽ ምክንያቶች ሳቢያ በስፋት እየተፈጸመ ያለ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች በርካታ ችግሮች ተጋላጭ እያደረጋቸው እንደሚገኝ ጥናቶች ያሳያሉ ብለዋል።

በተለይ የሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች በሚከሰትበት ወቅት ሴቶች፣ ሕፃናት፣ አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች ላይ የሚደርሰው ጾታዊ ጥቃት የከፋ እንደሆነ ባለፉት ጊዜያት በሀገራችን በተለይም በአፋር፣ በአማራ፣ በቤኒሻንጉል፣በትግራይና በኦሮሚያ ክልሎች የደረሰው ነባራዊ ሁኔታ ማሳያ ነው ያሉት አቶ ጌታቸው፤ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱም ከፌዴራል፣ ከክልሎችና ሌሎች ባለድርሻና አጋር አካላት ጋር በመሆን ጥቃትን ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ይሁን እንጂ በጾታዊ ጥቃት መከላከልና ምላሽ ሥራዎች ወጥ የሆነ ሀገራዊ የአሠራር ሥርዓት ባለመኖሩና ጥራቱን የጠበቀ ባለመሆኑ የሚሠሩ ሥራዎች ውጤታማነታቸው እምብዛም እንደሆነ ተናግረዋል።

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከአጋር ተቋማት ጋር በመተባበር ሀገር አቀፍ የአሠራር ሥርዓት ማዘጋጀቱን የገለጹት አማካሪው፤ መመሪያው ጾታዊ ጥቃትን ለመከላከል፣ተጋላጭነትን ለመቀነስ ፣እና ምላሽ አሰጣጥን ውጤታማነት ለማሳደግ ትልቅ አስተዋፅኦ ይኖረዋል ብለዋል።

መመሪያው በቀጣይ ወደ ክልሎች በማውረድ ተግባራዊ እንዲደረግ ስልጠናዎችና መመሪያውን የማስተዋወቅ ሥራ የሚሠራ መሆኑ በመድረኩ ተገልጿል።

መመሪያውን ተግባራዊ ለማድረግ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ፣የጤና ሚኒስቴር ፣የፍትህ ሚኒስቴር እንዲሁም ዩ ኤን ኤፍ ፒ ኤ የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመዋል።

# ማህበረሰቡ ነጻና ገለልተኛ የሆኑ እጩዎችን እንዲጠቁም ኮሚሽኑ ጥሪ አቀረበ

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን እጩ የሴቶችና ሕፃናት ምክትል ኮሚሽነር ለመምረጥ ማህበረሰቡ ነጻና ገለልተኛ የሆኑ እጩዎችን እንዲጠቁም ጥሪ አቀረበ፡፡

ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን እጩ የሴቶችና ሕፃናት ምክትል ኮሚሽነር ለመምረጥ የሕዝብ ጥቆማ ከትናንትናው እለት ጀምሮ ለአስራ አምስት ቀናት እንደሚካሄድ ኮሚሽኑ በሰጠው መግለጫ አስታውቋል፡፡

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ለሴቶችና ሕፃናት ኮሚሽነር እጩ አቅራቢ ኮሚቴ ፀሐፊ ወይዘሮ ባንቺይርጋ መለሰ በትናንትናው እለት በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር 210/1992 እና በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 1224/2012 መሠረት የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽንን አቋቁሟል፡፡

በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 210/1992 እና በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 1224/2012 መሠረት አንቀፅ 80(2) መሠረት ኮሚሽኑን የሚመሩ አንድ ዋና ኮሚሽነር፣ ምክትል ዋና ኮሚሽነር፤ አንድ የሴቶችና ሕፃናት ኮሚሽርና ሌሎች የዘርፍ ኮሚሽነሮች ተሹመው ሲሠሩ የቆዩ ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት ሥራ በለቀቁት የሴቶችና ሕፃናት ምክትል ኮሚሽነር ምትክ ማሟላት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ለዚህም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የእጩ አቅራቢ ኮሚቴ በማቋቋም ሥራውን በይፋ የጀመረ ሲሆን፤ የእጩ አቅራቢ ኮሚቴው የእጩ አቅራቢ ኮሚቴ ጽሕፈት ቤት በማቋቋም ሥራው የሚመራበት የምልመላ መስፈርት፣የድርጊት መርሀ ግብርና የትግበራ መመሪያ አዘጋጅቶ ወደ ሥራ ገብቷል ብለዋል፡፡

የእጩ አቅራቢ ኮሚቴው አወቃቀርም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ አቶ ታገሰ ጫፎ ሰብሳቢ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ምክትል ሰብሳቢን ጨምሮ ስምንት አባላትን የያዘ መሆኑንም ወይዘሮ ባንቺይርጋ ገልጸዋል፡፡

በመሆኑም በመላ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ ሕዝቦች ከሚያዚያ 7 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሚያዝያ 22 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ባሉት 15 ቀናት ዕጩዎችን በአካል፣ በጽሑፍ፣ ለዚሁ አላማ በተዘጋጁ ሳጥኖች እንዲሁም በኦንላይን መጠቆም የሚችል መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

እጩ አቅራቢ ኮሚቴውም በተከታታይ ተደማጭነትና ተነባቢነት ባላቸው የመገናኛ ዘዴዎች መስፈርቶች እንደሚገለጹ ወይዘሮ ባንቺይርጋ አስታውቀው፤ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥም እጩውን የመለየት ሥራውን በማጠናቀቅ ለምክር ቤት እንዲጸድቅ እንደሚቀርብ ተናግረዋል።



ወይዘሮ ባንቺይርጋ መለሰ

በዚህም መሠረት ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን የሴቶችና ሕፃናት ኮሚሽነር ለመሆን የሚጠቆመው ጾታ ሴት እጩዎች ሲሆኑ፤ ዜግነት ኢትዮጵያዊት እና ለኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት ተገዥ የሆኑ፣ ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ተቆርቋሪ የሆኑ፤ በሕግ ወይም አግባብነት ባለው ሌላ ሙያ የሠለጠኑ ወይም በልምድ ሰፊ እውቀት ያካበቱ፣ ሥራውን ለመሥራት የሚያስችል ጤንነት ያላቸው፣ ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ገለልተኛ የሆኑ፤ከደንበ መተላለፍ ውጪ በሌላ የወንጀል ጥፋት ተከሰው ያልተፈረደባቸው እና ዕድሜአቸው ከ35 ዓመት በላይ የሆኑ መሆን እንደሚኖርበት አስታውቀዋል፡፡

በመሆኑም ተቋም የሚገነባው በጠንካራ አመራር በመሆኑ ከላይ የተገለጹትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ነፃና ገለልተኛ የሆኑ እጩዎችን ከመላው የሀገሪቱ ሕዝቦች እንዲጠቁሙ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# የማምረቻ መሳሪያዎችን በሀገር ውስጥ የማምረት አቅም እየተፈጠረ ነው

## - በልማት እቅዱ መጨረሻ እስከ ዘጠኝ ቢሊዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዷል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ከውጪ የሚገቡ የማምረቻ መሳሪያዎችን በሀገር ውስጥ ማምረት የሚቻልበት አቅም እየተፈጠረ መሆኑን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ። በአስር ዓመቱ የልማት እቅድ መጨረሻ እስከ ዘጠኝ ቢሊዮን ዶላር ለማግኘት መታቀዱም ተገልጿል።

የማሽነሪ አምራች ኢንዱስትሪዎች ዕድሎች፣ ተግዳሮቶችና የቀጣይ የጋራ ሥራዎች ዙሪያ ከማሽነሪ አምራቾችና ባለድርሻ አካላት ጋር የውይይት መድረክ ትናንት ተካሂዷል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትር አቶ መላኩ አለበል በመድረኩ ላይ እንደገለጹት፤ ከውጪ ሲገቡ የነበሩ ማሽኖችና የማምረቻ መሳሪያዎችን በሀገር ውስጥ ማምረት የሚቻልበት አቅም እየተፈጠረ ነው።

የአምራች ዘርፉ ልማት በኢኮኖሚው መዋቅራዊ ሽግግር በማምጣት ፈጣን እድገት ለማስመዝገብ ይረዳል ያሉት አቶ መላኩ፤ በሀገር ውስጥ አምራቾች ተስፋ ሰጪ የማምረት አቅም እየተፈጠረ ነው ብለዋል።

የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉን እድገት ለማምጣት በመንግሥት ደረጃ ስትራቴጂዎችና ፖሊሲዎች ተግባራዊ እየተደረጉ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ የማሽነሪ ፖሊሲ፣የቆዳ ኢንዱስትሪን ጨምሮ፣ ገቢ ምርት መተካትና የአቅም ግንባታ ስትራቴጂዎች ተዘጋጅተው ወደ ሥራ መግባታቸውን ገልጸዋል።

በሀገሪቱ በአስር ዓመቱ የልማት እቅድ ወደ ውጪ የሚላከውን ምርት ለማሳደግ እየተሠራ መሆኑን የገለጹት አቶ መላኩ፤ ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ በአስር ዓመቱ የልማት እቅድ መጨረሻ እስከ ዘጠኝ ቢሊዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዷል ብለዋል።

በዘርፉ አምስት ሚሊዮን ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር መታቀዱን ጠቅሰው፤ የገቢ ምርትን ለመተካት 30 በመቶ የነበረውን የገበያ ድርሻ ወደ 60 በመቶ ለማሳደግ እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

የማምረት አቅም አጠቃቀምን ወደ 85 በመቶ ለማሳደግ መታቀዱን በመግለጽ በልማት እቅዱ አዳዲስ ኢንተርፕራይዞችን ለማቋቋም መካተታቸውን አመላክተዋል።

የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ልማት እሴት የተጨመረበት ምርት በማምረት ፈጣንና ዘላቂነት ያለው እድገት እንዲመዘገብ የሚያደርግ መሆኑን በመግለጽ፤ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ለማምጣትና የሥራ እድል በመፍጠር ወሳኝ ሚና እንዳለው ጠቁመዋል።

የሀገር ውስጥ ጥሬ እቃዎችን በመጠቀም ለአምራቾች ገበያ የሚፈጥር መሆኑን የገለጹት ሚኒስትሩ፤ ለኢንዱስትሪ ግብአት የሚሆኑ ማሽነሪዎች ምርትን በማሳደግ በኢኮኖሚው እድገት አዎንታዊ ሚና ይጫወታል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አለባቸው ንጉሴ በበኩላቸው፤ ማሽነሪ አምራቹን ከአምራች ኢንተርፕራይዞች እኩል በመደገፍ ለዘርፉ ልማት መሥራት አስፈላጊ ነው ብለዋል።

ባለፉት አምስት ዓመታት ከ32 ሺህ በላይ ማሽነሪዎች ለአምራች ኢንተርፕራይዞች በሊዝ ፋይናንስ ተላልፈዋል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ከውጪ የሚገቡት ማሽነሪዎችን በሀገር ውስጥ በመተካት በሂደት ሀገራዊ የማምረት አቅምን ለማሳካት የሚያስችል ነው ብለዋል።

የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍን ለመደገፍ ባለፉት ዓመታት በርካታ እንቅስቃሴዎች መደረጋቸውን ጠቅሰው፤ በተለይም ሀገራዊ የመልማት ፍላጎትን ለማሟላት እውቀትና ተግባር ተኮር እንቅስቃሴዎች እየተካሄዱ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

ባለፉት አምስት ዓመታት ከ15ሺህ በላይ አዳዲስ አምራች አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን መፍጠር ተችሏል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ከ16 ሚሊዮን ብር በላይ ብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል ብለዋል።

አምራቾች የመስሪያ ቦታዎችን እንዲያገኙ የመሠረተ ልማት አገልግሎት እንዲሟላላቸው መደረጉን ጠቅሰው፤ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት እንዲያገኙና በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገር የገበያ እድሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደረጉን አስረድተዋል።

# በክልሉ ከ5 ሺህ በላይ መኖሪያ ቤቶች ተገንብተው ለመምህራን ተላልፈዋል

**ዳግማዊት ግርማ**



አዲስ አበባ፡- በተያዘው በጀት ዓመት እስከ የካቲት ወር 2016 ዓ.ም ድረስ በገጠር የክልሉ አካባቢዎች ለሚገኙ ከአምስት ሺህ 508 በላይ ቤቶች ተገንብተው ለመምህራን መተላለፋቸውን የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ አስታወቀ፡፡

በበጀት ዓመቱ በክልሉ ሦስት ሺህ 410 ትምህርት ቤቶችን ለማደስ ታቅዶ የአራት ሺህ 627 ትምህርት ቤቶችን የማሻሻያ ሥራ በማጠናቀቅ ከእቅድ በላይ አፈጻጸም መመዝገቡ ተመላክቷል፡፡

በትምህርት ቢሮው በምክትል ኃላፊ ደረጃ የዋና ኃላፊው አማካሪ ኤፍሬም ተሰማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በኦሮሚያ ክልል የመምህራንን ምቾት ለመጠበቅና የመማር ማስተማር ሥራውን ውጤታማ ለማድረግ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል፡፡

በገጠራማ የክልሉ አካባቢዎች ለሚያገለግሉ መምህራን በየትምህርት ቤቶቻቸው ውስጥ ከአምስት ሺህ 500 በላይ ቤቶች መኖሪያ ተገንብቶላቸዋል ሲሉ አስረድተዋል።

ከዚህ ቀደም በገጠራማ የክልሉ ክፍሎች ያሉ መምህራን ሥራቸውን አከናውነው ሲጨርሱ የሚያርፉባቸውን አራት ሺህ የመምህራን መኖሪያ ለመገንባት መታቀዱን አስታውሰው፤ አምስት ሺህ 508ቱን ቤቶች አጠናቆ በማስተላለፍ ከዕቅድ በላይ አፈጻጸም መመዝገቡን አመላክተዋል።

የመምህራኑ መኖሪያዎች የትምህርት ቤቶቹ ንብረት በመሆናቸው የሥራ ዝውውር ቢፈጸም እንኳን በማንኛውም ጊዜ ወደ ትምህርት ቤቶች የሚመደቡ መምህራን እንደሚጠቀሙባቸው አቶ ኤፍሬም አንስተዋል፡፡

በከተሞች አካባቢ የሚገኙ መምህራን ደግሞ የመኖሪያ ቤት መሥሪያ ቦታ እንዲሰጣቸው በክልሉ ፕሬዚዳንት አማካኝነት የወረደ መመሪያ መኖሩን ያነሱት አቶ ኤፍሬም፤ በተወሰኑ ከተሞች ላይ በማህበር እያደራጁ የቤት መሥሪያ ቦታዎች የመስጠቱ ሂደት መቀጠሉን ጠቅሰዋል፡፡

መምህራን በምቹ ሁኔታ ውስጥ ሆነው እንዲሠሩ ለማገዝ የሚደረገው ጥረት እንደሚቀጥል ጠቁመው፤ መምህራን በየትምህርት ክፍሎቻቸው በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ብቃታቸውን የሚያሳድጉ ስልጠናዎችን እያገኙ መሆኑን ተናግረዋል።

ስልጠናዎቹ መምህራኑ በየትኛውም ዘርፍ ላይ ክፍተት አለባቸው የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ እንደሚረዱ ገልጸዋል።


በአጠቃላይ የትምህርት ተደራሽነትና ጥራትን በሚመለከት በክልሉ በርካታ ተግባራት መከናወናቸውን አመላክተው፤ በበጀት ዓመቱ ሦስት ሺህ 410 ትምህርት ቤቶችን ለማደስ ታቅዶ ከእቅድ በላይ አፈጻጸም በማስመዝገብ 4 ሺህ 627 ያህሉ ላይ የማሻሻያ ሥራዎችን ማከናወን ተችሏል ብለዋል።

በተጨማሪም በክልሉ 300 ሰዎችን አሳድሮ ማሰልጠን የሚያስችል ማዕከል መዘጋጀቱን ጠቁመው፤ የሰው ኃይልና አስፈላጊውን ግብዓት በማሟላት በሪፎርም ሂደቱ በክልሉ የሚገኙ አንድ ሺህ 100 ሱፐርቫይዘሮችን በማሰጠልን ስምሪት መሰጠቱን አስታውቀዋል።

# ባለፉት ዘጠኝ ወራት 100 ሺህ ሄክታር መሬት ለመስኖ ዝግጁ ሆኗል

## - በኢትዮጵያ 10 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በመስኖ ሊለማ ይችላል

**ቃልኪዳን አሳዬ**



የርብ መስኖ ግድብ

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ዘጠኝ ወራት 100 ሺህ ሄክታር መሬት ለመስኖ ልማት ዝግጁ ማድረግ መቻሉን የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነት እና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ አቶ ብዙነህ ቶልቻ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በ2016 ዓ.ም በጀት ዓመት በመላው ሀገሪቱ 391 ሺህ ሄክታር መሬት ለመስኖ ልማት ዝግጁ ለማድረግ እቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው፡፡

እንደ አቶ ብዙነህ ገለጻ፤ በሁሉም ክልሎች የመካከለኛና አነስተኛ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶችን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ክትትል እያደረገባቸው ይገኛል፡ ፡ በተደረገው የድጋፍና ክትትል ሥራም ባለፉት ዘጠኝ ወራት በመላው ሀገሪቱ 100ሺህ ሄክታር መሬት ለመስኖ ልማት ዝግጁ ማድረግ የተቻለ ሲሆን፤ ስፍራውን የማልማትና አዝርዕት የመዝራቱ ሥራ በግብርና ሚኒስቴር የሚከናወን ነው፡፡

በፌዴራልና በክልሎች በመጠናቀቅ ላይ ያሉ በርካታ ፕሮጀክቶች በመኖራቸው አብዛኛው ውጤት ሊመዘገብ የሚችለው በበጀት ዓመቱ ማጠቃለያ ላይ እንደሚሆን የገለጹት አቶ ብዙነህ፤ ባለፉት ዓመታት በዓለም ባንክ ድጋፍ በተከናወኑ ጥናቶች በኢትዮጵያ 10 ሚሊዮን ሄክታር የሚደርስ መሬት በመስኖ መልማት እንደሚችል መታወቁን ጠቁመዋል፡፡

በዚህም ባለፉት ሦስት ዓመት ተኩል ጊዜያት በአጠቃላይ በሀገሪቱ በመስኖ መሠረተ ልማት ግንባታ ከ1 ነጥብ 6 ሚሊዮን በላይ ሄክታር መሬት ለልማት ዝግጁ ማድረግ ተችሏል ብለዋል፡፡

አቶ ብዙነህ እንደሚናገሩት፤ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ 28 የመስኖ መሠረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች እያከናወነ ሲሆን፤ በተያዘው በጀት ዓመት 12 ፕሮጀክቶችን በከፊል በማጠናቀቅ ከ29 ሺህ በላይ ሄክታር መሬት ለመስኖ ልማት ዝግጁ ለማድረግ እቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው፡፡

ባለፉት ሦስት ዓመት ተኩል ጊዜያት ከ1 ነጥብ 3 ሚሊዮን በላይ ሄክታር መሬት የጥናትና ዲዛይን ሥራ ተሰርቶ ለመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ግንባታ ዝግጁ ማድረግ መቻሉን ጠቁመው፣ በጀት ሲገኝ ግንባታው እንደሚከናወን ገልጸዋል።

በተያዘው በጀት ዓመት በመላው ሀገሪቱ 353ሺህ 630 ሄክታር መሬት ጥናትና ዲዛይን ሥራ በመሥራት ለመስኖ ልማት ዝግጁ ለማድረግ እቅድ ተይዞ እየተሠራ እንደሚገኝና እስካሁን ባለው አፈጻጸም ከ70ሺህ ሄክታር በላይ መሬት የጥናትና ዲዛይን ሥራ በመሥራት ለመስኖ ልማት ዝግጁ ማድረግ መቻሉንም አቶ ብዙነህ አንስተዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት 25 የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች የጥናትና ዲዛይን ሥራ እየተከናወነ መሆኑን የገለጹት አቶ ብዙነህ፤ ከእነዚህ መካከል የኤረር፣ የሎኮ አባያ፣ የደቡብ ጎዴ፣ የታችኛው ገናሌና ሌሎችም እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ እንደሚጠናቀቁ ተናግረዋል፡፡

# “ኢትዮጵያ በቀጣናው የውሃ ሀብትን በፍትሐዊነት መጠቀም እንዲቻል ሰፊ ተግባራት እያከናወነች ነው”

- ኢንጂነር ጌድዮን አስፋው
የዓባይ ግድብ ቴክኒካል ቡድን ተደራዳሪ

ልጅዓለም ፍቅሬ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በቀጣናው የውሃ ሀብቶችን በፍትሐዊነትና በእኩልነት መጠቀም እንዲቻል ሰፊ ተግባራት እያከናወነች ነው ሲሉ የዓባይ ግድብ ቴክኒካል ቡድን ተደራዳሪ ኢንጅነር ጌድዮን አስፋው ገለጹ፡፡

የዓባይ ግድብ ቴክኒካል ቡድን ተደራዳሪ ኢንጂነር ጌድዮን አስፋው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ኢትዮጵያ በቀጣናው የውሃ ሀብትን በፍትሐዊነትና በእኩልነት መጠቀም እንዲቻል ሰፊ ሥራዎች እየሠራች ነው፡፡

ኢንጂነር ጌድዮን አክለውም፤ የውሃ ሀብት ላይ ያለውን የጋራ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚደረጉ ትብብሮችን እውን ለማድረግ የሀገሪቱ የተለያዩ የሥራ ኃላፊዎች ወደ ተፋሰሱ ሀገራት ጉዞ በማድረግ ስለጉዳዩ ለማብራራት የሄዱበት ርቀት ለዚህ ማሳያ ነው ብለዋል፡፡

80 በመቶ የሚሆኑት የሀገሪቷ ወንዞች ድንበር ተሻጋሪ ናቸው ያሉት ኢንጂነር ጌድዮን፤ ከዚህ አኳያ ከታችኛው ተፋሰስ ሀገሮች ጋር በሃይድሮ ዲፕሎማሲ ውስጥ መሳተፍም እንደሚጠይቅ አብራርተዋል፡፡

ለአብነትም ጊቤ፣ ባሮ አኮቦ፣ አዋይና ተካዜ ወንዞች ከሶማሊያ፣ከኬንያ፣ ከሱዳን፣ ከደቡብ ሱዳንና ከግብፅ ጋር ቢጋራ ሀገሪቷ የምትጋራቸው ወንዞች መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

እስካሁን በተደረጉ ዲፕሎማሲያዊ ሥራዎች አብዛኞቹ የተፋሰሱ ሀገራት አብሮ ለመሥራት በሚያስችለው የትብብር ማዕቀፍ ተባባሪ እየሆኑ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

እንደ ኢንጂነር ጌድዮን ገለጻ፤ የትብብር ስምምነቱ ያለፈውን የቅኝ ግዛት የውሃ ላይ ስምምነቶችን በአዲስ የስምምነት ማዕቀፍ የሚተካ ነው፡፡ ይህም በኢትዮጵያ በኩል የተሳካ ዲፕሎማሲ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

ግብጽ በቅርቡ በውጪ ጉዳይ ሚኒስትሯ በኩል የዓባይ ግድብ ድርድር መቋረጡን ብታስታውቅም ኢትዮጵያ እንደ ሁልጊዜው ለውይይትና ያልተፈቱ የቴክኒክ ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ፈቃደኛ እንደሆነች አስረድተዋል፡፡



ከወሰን ተሻጋሪ ወንዞች ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ ቀጣናዊ ትብብሮችን በማጎልበት ሀብቶችን በፍትሐዊነትና በእኩልነት የውሃ ፖሊሲ እየተከተለች ነው ያሉት ኢንጂነር ጌድዮን፤ ይህም ሲጋራ ተጠቃሚነት የምታከናውናቸው በጎ ተግባራትን የሚያሳዩ መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡

እንደ ኢንጂነር ጌድዮን ገለጻ፤በውሃ ዲፕሎማሲ የላቀ ውጤት ለማስመዝገብ ዩኒቨርሲቲዎች፣ዲያስፖራው እንዲሁም ወጣቱ የውሃ ፖሊሲ፣ስትራቴጂና የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ላይ መሥራት ይገባቸዋል፡፡ በተጨማሪም ለወጣት ባለሙያዎች አስፈላጊውን ስልጠና በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር መስጠት እንደሚገባና ለዚህም መንግሥት አስፈላጊ እርምጃ መውሰድ እንዳለበት አመላክተዋል፡፡

## በአማራ ክልል...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የስልጠና እና የተባይ መከላከያ ኬሚካል እንዲሁም አስፈላጊ የሆኑ የግብርና ግብዓቶች በሙሉ እንዲሟሉ መደረጉን ተናግረዋል።

ይህ ድጋፍ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ እና እያደገ በመምጣቱ አርሶ አደሩ በመስኖ መሬት ላይ ከሁለት ጊዜ በላይ ማልማት እንዲችል አድርጓል ያሉት አቶ ተሻለ፤ ይህም በክልሉ የሚለማው የበጋ መስኖ ስንዴ የመሬት ሽፋን እንዲያድግ እና ምርታማነት እንዲጨምር ማድረጉን ገልጸዋል።

በአማራ ክልል በዘንድሮ የበጋ መስኖ ስንዴ ከዘጠኝ ነጥብ አራት ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ይገኛል ያሉት አቶ ተሻለ፤ የፀጥታ ችግር ባለባቸው ማለትም በጎንደር፣ ጎጃም እና በአንዳንድ የክልሉ አካባቢዎች የበጋ መስኖ ስንዴን ማልማት አልተቻለም። ይህም የምርት መጠኑ እንዲቀንስ አድርጎታል ብለዋል።

እንደ አቶ ተሻለ ገለፃ፤ ቢሮው በክልሉ ከ250 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በበጋ መስኖ ስንዴ ለማልማት አቅዷል። ነገር ግን በክልሉ ባለው የፀጥታ ችግር ሁሉንም መሬት ማልማት አልተቻለም። በቀጣይ ዓመት አርሶ አደሩ በበጋ መስኖ ስንዴ ከፍተኛ ውጤት እንዲያመጣ ጠንካራ ቅድመ ዝግጅት ይደረጋል። ይህም ክልሉ በበጋ መስኖ ስንዴ የሚያለማውን የመሬት መጠን ያሳድጋል።

በአማራ ክልል የበጋ መስኖ ስንዴ ማልማት የተጀመረው በ2013 ዓመተ ምህረት ሲሆን፤ በዚህም በየዓመቱ የሚለማው መሬት እና የሚገኘው ምርት እያደገ መምጣቱ ብለዋል።

## ከቱሉ ቦሎ እስከ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ያሉትን አውራ መንገዶች እንደሚያገናኝ አመልክተዋል።

የመንገድ ሥራው የቻይናው ዓለምአቀፍ ሥራ ተቋራጭ በሁናን ሁንዳ ሮድ ኤንድ ብሪጅ ኮርፖሬሽን እየተከናወነ ሲሆን፤ የግንባታ ጥራት እና ቁጥጥሩ በተባበሩት የምህንድስና አማካሪዎች ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ እየተሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

መንገዱ ሲጠናቀቅ የሚሰጠው ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ የጎላ እንደሆነ የገለጹት ሥራ አስኪያጁ፤ አካባቢው ላይ በስፋት የሚመረቱ ምርቶች ጤፍ፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ ባቄላ እና እንስሳት ወደ ማዕከል ገበያ በማቅረብ ገበሬው የተሻለ የኢኮኖሚ አቅም እንዲኖረው ዕድል እንደሚፈጥር አስረድተዋል።

በተጨማሪም ይህ ደረጃውን የጠበቀ መንገድ ማህበራዊ መስተጋብሩን በማሳለጥ የጤና፣ትምህርት እና መሰል ተቋማት ተደራሽነታቸው በእጅጉ እንዲጨምር እንደሚያደርግም አብራርተዋል።

የፕሮጀክቱ ሙሉ ወጪ በፌዴራል መንግሥት የተሸፈነ ሲሆን፤ የመንገድ ግንባታውን በስድስት ወራት ውስጥ ለማጠናቀቅ እየተሠራ ይገኛል ብለዋል።

የቀረውን ሥራ በፍጥነት ለመጨረስ እንቅፋት የሆኑትን በሁለቱም ከተሞች (ቱሉቦሎ እና ኬላ) ያልተነሱ የውሃ መስመሮች፣ የኤሌክትሪክ መስመሮች፣እና መኖሪያ ቤቶች እንዲነሱ ለማድረግ ጥረት ማድረግ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

የፕሮጀክቱ ተጠሪ መሐንዲስ የሆኑት አቶ መኮንን ከበደ በበኩላቸው፤የመንገድ ሥራው 95 በመቶ መጠናቀቁን በመግለፅ፤ ከመንገድ ግንባታው ጋር ሦስት ጥራታቸውን የጠበቁ ድልድዮች መገንባታቸውን ተናግረዋል።

ፕሮጀክቱ ከተያዘለት በጀት የስምንት ሚሊዮን ብር ጭማሪ ማሳየቱን የገለጹ ሲሆን፤የዚህም ምክንያት የአዳጅ ዋጋ መናር እና ጥራት ያላቸው ማቴሪያሎች በየጊዜው በሚያሳዩት የዋጋ ጭማሪ እንደሆነ አስረድተዋል።

## አረንጓዴው...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ስሙን የሰጠኝ የድሬዳዋ ሕዝብ ነው የሚሉት አቶ በያን፤ ቀደም ሲል የጋርፍ መውረጃና ቆሻሻ መጣያ የነበረ ሁለት ሄክታር መሬትን ከ20 ሺ በላይ ችግኝ በማልበስ ወደ ጫካነት መቀየር ችለዋል።

ችግኞችን ለመትከል የተነሳሱበት ዋነኛው ምክንያት በ1998 ዓ.ም. በድሬዳዋ ተከስቶ የነበረው የጎርፍ አደጋ ነው፡፡ አንድ ቀበሌን ምድረ በዳ ባደረገው በዚያ ጎርፍ ሰባት የቅርብ ቤተሰቦቻቸውን አጥተዋል፡፡ የአጎታቸው ልጅ ሁለት ልጆቹን ዛፍ ላይ ይዞ በመውጣት ህይወታቸውን ማትረፍ ስለቻለ፣ ዛፍ ቢኖር ኖሮ ብዙ ሰው ሊድን ይችል ነበር የሚል ነገር በአእምሯቸው እንደተቀረጸም ይገልጻሉ፡፡

በ2000 ዓ.ም. መንግሥት ለአንድ ዜጋ ሁለት ችግኝ የሚል ዘመቻ ሲጀምር ሁለት ሺ ችግኝ መጠየቃቸውን የሚያወሱት አረንጓዴው ሰው፣ ችግኞቹን አግኝተው “ነምበር ዋን” በሚባለው አካባቢ ሁሉንም በአንድ ቀን መትከላቸውን ይናገራሉ፡፡

“የተከልኩት ሁሉ ስለሚበቅልልኝ ቢሊዮን ብር ካላቸው ሰዎች በላይ እኔ ደስተኛ ነኝ፡፡ እስካሁን ድረስ 650 ሺ ችግኞችን አፍልቼ ተክያለሁ፤ ለሰዎችም አከፋፍያለሁ” የሚሉት አቶ በያን፤ አላህ ዕድሜ ከሰጠኝ ሦስት ሚሊዮን አራት መቶ ሺ ዛፍ በመትከል በሦስት ሚሊዮን ችግኝ የዓለምን ሪከርድ የያዙትን ኬኒያዊቷን ዋንጋሪ ማታይ መቅደም እፈልጋለሁ፡፡ ይህንን የዓለም ሪከርድ በእርግጠኝነት እስር ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አሳካዋለሁ ሲሉ ህልማቸውን ይገልጻሉ፡፡

በተከሏቸው ከ20 ሺ በላይ ዛፎች የተፈጠረውን አረንጓዴ ስፍራ “ኢለናም” ፓርክ ብለው ይጠሩታል፡ ፡ ስያሜው ሁለት ትርጉሞች እንዳሉት የሚጠቁሙት አቶ በያን፤ አንደኛ “ኢትዮጵያ ለምለም ናት ምንጊዜም” በምህረፃር-ቃል ሲጻፍ (ኢለናም) ይሆናል፤ ሁለተኛ ደግሞ ቃሉ በቀቤና ብሔረሰብ ቋንቋ “ያሰብንበት እንደርሳለን” ማለት እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ የመጨረሻ ልጃቸውንም ኢለናም ብለው ነው የጠሯት፡፡

ላለፉት 17 ዓመታት ራሴን ለዚህ ደን ልማት ሰጥቻለሁ፡፡ እኔ የፈጠርኩት ጫካ ዛሬ የድሬዳዋ ሳንባ ሆኖ ሳየው ልዩ ደስታ ይሰማኛል፡፡ በቀጣይም የከተማ አስተዳደሩ ኣብሮኝ ከሠራ ድሬዳዋ ውስጥ በዘጠኙም ቀበሌዎች ትናንሽ አማዞኖችን መፍጠር እችላለሁ ይላሉ፡፡

ፓርኩ ውስጥ ቀጥረው ለሚያሰሯቸው አራት ሠራተኞች በወር 18 ሺ ብር ደመወዝ ይከፍላሉ፡፡ ለሠራተኞቹ የሚከፍሉትን ገንዘብ ከየት እንደሚያገኙ ሲናገሩ፣ “አንዳንድ ጊዜ ችግኝ የሚገዙ ሆቴሎች፣ ድርጅቶችና ግለሰቦች ሲመጡ የሚገኘውን ገቢ እስቀምጬ እየቆጠርኩ እንዲሁም አንዳንድ በጎ አድራጊዎች በሚያደርጉልኝ ድጋፍ እና በልጆቼ እርዳታ ነው፤ ከችግኝ ሥራ ገንዘብ አትጠብቅም”ይላሉ፡፡

አንድን አካባቢ በሦስት ዓመታት ውስጥ ደን ማድረግ እችላለሁ የሚሉት አረንጓዴው ሰው፣ መትከያ ቦታ ከተዘጋጀላቸው ከድሬዳዋ ውጭ በሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች የትም ቦታ ሔደው ችግኞች መትከል እንደሚፈልጉ ጠቁመው፣ ቦታ ካገኘሁ እንጦጦስ የሚባለውም ስፍራ ሄጄ ቢሆን ችግኝ መትከል እፈልጋለሁ ሲሉ ይቀልዳሉ፡፡

አቶ በያን ወደ ደን ልማት እንዲገቡ ምክንያት የሆናቸው ባለታሪክ የአጎታቸው ልጅ አቶ መሐመድ በበኩላቸው፣ “በ1998 ጎርፍ ተጠቂ ነኝ፡፡ ጎርፉ ባለቤቴንና ሁለት ልጆቼን ወስዶብኛል፡፡ ሁለት ወንድ ልጆቼን ዛፍ ላይ ሰቅዬ ነብሳቸውን አትርፌያለሁ፡፡ በወቅቱ ሀዘን የተቀመጥኩት አቶ በያን ቤት ነበር” ሲሉ አጋጣሚውን ያስታውሳሉ፡፡

ከክስተቱ በኋላ አቶ በያን ዛፍ የሰውን ልጅ ህይወት ያድናል በሚል ችግኝ መትከል መጀመራቸውን የሚመሰክሩት አቶ መሐመድ፣ በወቅቱ ብዙ ሰዎች አቶ በያን ነጭ አሸዋ ላይ ዛፍ እተክላለሁ ብሎ የተነሳው ምን ነክቶት ነው ይሉ ነበር፡፡ ያ በነጭ አሸዋ የተሞላ ሜዳ ዛሬ በደን ተሸፍኖ ሲታይ ይደንቃል፤ እርሱንም በጣም ጠንካራና ተምሳሌት የሆነ ሰው ያደርገዋል በማለት አድናቆታቸውን ይገልጻሉ፡፡

አቶ በያን የሦስት ወንድና የሦስት ሴት ልጆች አባት ናቸው፡፡ የመጨረሻ ልጃቸው ኢለናም በያን የአባቷን አርአያነት ተከትላ ለችግኞች የተለየ ፍቅር አድሮባታል፡፡ አሁን የ15 ዓመት ታዳጊ ናት፡፡ ከዕጽዋት ቅጠላ ቅጠልና ስራስር መድኃኒቶችን በባህላዊ መንገድ እንደሚቀምሙ የሚናገሩት አቶ በያን፣ ይህን እውቀታቸውን እያወረሱ ያሉት ለመጨረሻ ሴት ልጃቸው እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡

“ዛፍ ትክሉ ከፍቷል ዘመኑ” የሚል መፈክራቸውን በተለያዩ ቋንቋዎች በቃላቸው የሚወጡት አረንጓዴው ሰው ፈተና የሆነባቸውን ነገር ሲገልጹ፣ የእኔ መሠረታዊ ችግር ውሃ ነው፡፡ በበጎ ፈቃደኞች ጥናት አስጠንቼ በ52፣ 68 እና በ80 ሜትር ርቀት በተለያዩ ቦታዎች ውሃ እንደሚገኝ ተረጋግጧል፡፡ ያለብኝ የውሃ ችግር ቢፈታልኝ ሦስት ሚሊዮን አራት መቶ ሺ ችግኞች የመትከል ዕቅዴን ባጠረ ጊዜ ማሳካት እችላለሁ ይላሉ፡፡

አረንጓዴው ሰው በ2014 ዓ.ም ዓለም አቀፍ የአረንጓዴ ቀን ሲከበር በፌዴራል መንግሥት የአረንጓዴ አምባሳደር የሚል ሰርቲፍኬት ተበርክቶላቸዋል፡፡ ከአካባቢ ጥበቃ፣ ከጽዳትና ውበት እንዲሁም ከተለያዩ ድርጅቶችም እውቅና ተሰጥቷቸዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት የተገኘው ውጤት የሀገራዊ ብልጽግና አይቀሬነት ማሳያ ነው!

ኢትዮጵያ በምግብ ራሷን ለመቻልም ሆነ፣ በ2030 መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ጎራ ለመካተት የሚያስችሏትን ተግባራት እያከናወነች ትገኛለች፡፡ ለዚህም በግብርናው፣ በማዕድን፣ በንግድና ኢንቨስትመንት፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ በፋይናንስ እና በሌሎችም መስኮች እየሠራች ባለችው ሥራ አበረታች ውጤት እያስመዘገበች ነው፡፡

አንድ ሀገር ደግሞ ነጻነትና ሉዓላዊነቷ የተሟላ ሆኖ የሚቀጥለው፤ ያ ሀገር ቢያንስ መሠረታዊ የሚባሉ ጉዳዮቹን በራሱ መከወን የሚችልበትን ዕድል መፍጠር ሲችል ነው፡፡ በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ የሀገር አንድነትና ነጻነቷን ያዘለቀችበትን የአውደ ግንባር ገድል የፈጸመች ቢሆንም፤ ይሄ በዋጋ የተገኘው ነጻነቷ ግን በኢኮኖሚው መስክ ባላት ደካማ አቅም ምክንያት ሲፈተን ኖሯል፡፡

ይሄን የሚፈትን ነጻነት ይዞ ደግሞ እንደ ሀገር የሚፈለገውን ሁሉን አቀፍ ብልጽግና እውን ማድረግ አይቻልም፡፡ በመሆኑም ቢያንስ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ተግባር መሆኑ ታምኖበት በዚህ ላይ በሚገባ ተሠርቷል፡፡ እናም ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ ስንዴን ከውጪ ማስገባት እንድታቆም ብቻ ሳይሆን፤ ከራሷ አልፋ ለሌሎች ስንዴን ማቅረብ የቻለችበትን ተግባር አከናውናለች፡፡

በዚህ ረገድ በተለይ ከለውጡ ማግስት በዝናብ ላይ ጥገኛ ሆኖ ከዘለቀው የኢትዮጵያ ግብርና የተሻገረ ሥራን መሥራት ተችሏል፡፡ የበጋ መስኖ ልማት ደግሞ ከእነዚህ ተግባራት መካከል ግንባር ቀደሙ ነው፡፡ ምክንያቱም በመስኖ የሚለማ ሰፊ መሬት እና ይሄንን መሬት ማልማት የሚችሉ ዓመቱን ሙሉ የሚፈስሱ ወንዞች ያሏት ኢትዮጵያ፤ ይሄንን አቀናጅታ ዜጎቿን መመገብ የምትችልበትን አቅም መፍጠር ተችሏል፡፡

ቀደም ሲል ያውም በተበጣጠሰ መልኩ በአስር ሺዎች ሄክታር ላይ ብቻ ይከናወን የነበረውን የመስኖ ልማት ሥራ፤ ዛሬ ላይ በሚሊዮኖች በሚቆጠር ሄክታር መሬት ላይ መተግበር ተችሏል፡፡ በዚህም ከሺዎች ወደ ሚሊዮኖች ኩንታል ምርት ማግኘትም አስችሏል፡፡ ይሄው ተግባር ነው ኢትዮጵያን ስንዴ ከመለመን ወደ መስጠት፤ ስንዴን ከመሸመት ወደ መሸጥ እንድትሸጋገር ያደረጋት፡፡

ከሰሞኑ ከግብርና ሚኒስቴር የወጣ መረጃ እንዳመለከተው ደግሞ፤ በዘንድሮው የበጋ መስኖ ልማት ሦስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ለማልማት ውጥን ተይዞ፤ ሦስት ሚሊዮን ሄክታር በዘር ተሸፍኗል፡፡ ከዚህም ወደ 120 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ለማግኘት ታቅዷል፡፡

ከሦስት ሚሊዮን ሄክታሩ ላይ ይገኛል ተብሎ ከታቀደው 120 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ውስጥም እስከ መጋቢት 30 ቀን 2016 ዓ.ም በአንድ ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ሄክታር ላይ ያለው ሰብል ተሰብስቦ፤ ከ58 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ተገኝቷል፡፡ ቀሪው ሰብል የመሰብሰብ ሥራም ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡

በዘርፉ እየተከናወነ ያለው ተግባርም ሆነ እየተገኘ ያለው ውጤት ደግሞ የግብርና ምርትን በአይነትና በመጠን ከማሳደግ አኳያ ከፍ ያለ ሚና ያለው ሲሆን፤ የዜጎችን የምግብ ሥርዓት ለማሻሻልም ሆነ እንደ ሀገር የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚደረገው ጥረት ከግቡ እንዲደርስ የማይተካ ድርሻ አለው፡፡

በዚህ መልኩ በበጋ ስንዴ የታየውን ውጤት የበለጠ ከፍ ለማድረግ የሚያስችሉ ሌሎች ተግባራት እየተከናወኑ መሆናቸው ደግሞ፤ እንደ ሀገር የተሟላ ነጻነትንም፣ ብልጽግናንም እውን ለማድረግ ያለውን የመንግሥት ቁርጠኝነት የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በተለይ በአረንጓዴ ዐሻራም ሆነ በሌማት ትሩፋት ሥራዎች ያሉ ጅምሮችና ውጤቶቻቸው የዚህ ማሳያ ናቸው፡፡

ለምሳሌ፣ ከስንዴ ባሻገር በሩዝ፣ በአረንጓዴ አሻራ፣ በእንስሳት እርባታና የእንስሳት ተዋፅኦዎች፣ በሻይ፣ በአትክልትና ፍራፍሬ፣ ዘርፎች የተሰሩትም፣ እየተሰሩ ያሉትም ሥራዎች በውጤት የታጀቡ ናቸው፡፡ እነዚህ ደግሞ ኢትዮጵያ በምግብ ራሷን በመቻል ቢያንስ ለርዳታ የሚዘረጉ እጆቿ ጫና ከመዳረግ ወጥተው፤ ከራሷ አልፋ ለሌሎች ድጋፍ ማድረግ የምትችልበትን ሙሉ ነጻነት የሚያጎናጽፏት ናቸው፡፡

ከዚህ ባሻገር ግን፣ ይሄ ነጻነቷ የሚፈጥርላት ከፍ ያለ የማድረግም ሆነ የመደመጥ አቅም አለ፡፡ ይሄ አቅም ደግሞ የራሷን የልማት ሃሳብና ንድፍ ወደ ተግባር ለመቀየር በምታደርገው ጥረት ውስጥ ቢቻል ደጋፊ ኃይሎችን ለማሰባሰብ፤ ባይቻል ግን እጇን ሊጠመዝዛት የሚዳዳ ኃይል እንዳይኖር ማድረግ ያስችላታል፡፡ እናም አሁን ላይ በበጋ መስኖ የስንዴ ልማቱም ሆነ እሱን ተከትለው እየተመዘገቡ ካሉ ውጤቶች መረዳት የሚቻለው፤ እንደ ሀገር ተባብሮ እና በሙሉ አቅም ተግቶ መሥራት ከተቻለ እውን እንዲመጣ የሚፈለገው የተሟላ ብልጽግናን ከመሳካት የሚያግደው ነገር እንደሌለ ነው!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
• ኃይሉ ሣህለድንግል
• እስማኤል አረቦ
• ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ለደንበኞች ክብሬታ ሳለው አገልግሎት እንትጋ

ከትዝታ ማስታወሻ

ድሮ ድሮ በፌስታሎች ላይ ሳይቀር "ደንበኛ ንጉስ ነው" የሚል ጽሁፍ መመልከት የተለመደ ነበር:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የደንበኛ ንጉስነት ተቀይሮ ይሆን ወይም በሌላ፣ ቢያንስ ጽሑፎቹን ማየት እየቀረ ነው:: በሀገራችን ደንበኛን ያማከለ አገልግሎት ከመስጠት አንጻር የግል ድርጅቶች በአንጻራዊነት የተሻሉ ናቸው::

ምንም እንኳን ከሀገራችን አንጻር የተሻሉ የተባሉት የግል ድርጅቶችም ቢሆኑ ካደጉት ሀገራት አንጻር ካየናቸው ብዙ የሚቀረን ነገር እንዳለ ሳይታለም የተፈታ ሀቅ ነው:: በውጭ ሀገራት ድርጅቶች ደንበኛ ለገዛው እቃ መመለሻ በርካታ ጊዜ ከመኖሩም በላይ "የገዛሁት እቃ አልተመቸኝምና ገንዘቤን መልሱ" ተብሎ ለሚቀርብለት ጥያቄ ምላሹ "ምን እናሻሽል" እና "ለፈጠርንብዎ አለመመቸት ይቅርታ" የሚል ነው::

እኛ ሀገር ግን በተቃራኒው ነው፤ በአብዛኞቹ የመሸጫ ቦታዎች "የተሸጠ እቃ አይመለስም" የሚል በጉልህ የሰፈረ ጽሑፍ መመልከት አዲስ አይደለም:: ምነው ቢሉ "የቤቱ ሕግ ነው"፤ በጣም የተሻለ ደንበኛ ያስተናግዳሉ ከተባለ እቃውን በሌላ እቃ መለወጥ ቢተባበሩ ነው:: እሱንም ቢሆን መጀመሪያ የተወሰደው እቃ ዋጋው እንደሚቀንስ በመንገር ለተመሳሳይ እቃ የዋጋ ጭማሪ መጠየቅ የተለመደ ሆኗል::

ያም ቢሆን በአንጻራዊነት የደንበኛ አያያዝ ጉዳይ በግል ተቋማት የተሻለ እንደሆነ ይነገራል:: በአብዛኛው የመንግሥት ተቋማት ንጉሱ ደንበኛው ሳይሆን እንዲያገለግል የተቀመጠው አካል መሆኑን በርካቶች በምሬት ያነሱታል:: ለዚህም መጉላላቱም ሆነ ፊት መነሳቱ የሚጀምረው የአገልጋዩን፣ የተገልጋዩን እንዲሁም የተቋሙን ደህንነት እንዲጠብቁ ከተመደቡ መግቢያ በር ላይ ከሚገኙ የጥበቃ አባላት ይጀመራል::

የእነሱን ማመነጫጨቅ አልፎ የሚመለከተው አካል ጋ የደረሰ ባለጉዳይ "ስብሰባ ላይ" እንደሆኑና መቼ እንደሚመለሱ እንደማይታወቅ ይነገረዋል:: "ለምን?" የማለት መብት የለውም:: በአብዛኛው ከቢሮ የሚወጡ ባለሙያዎችም ሆኑ አመራሮች ሰው ወክሎ ያለመሄድ ችግር ይስተዋልባቸዋል::

በዚህ የተነሳ ባለጉዳይ የግልም ሆነ የመንግሥት ሥራውን እየተወ መመላለስ ግድ ይለዋል:: ያኔ ታዲያ በር አካባቢ ለሚያንዣብቡና "ጉዳያችሁን በአጭር እንድንጨርስላችሁ ክፈሉ" ለሚሉ ደላሎች ይጋለጣል:: እነዚህ ጩልሌዎች እውነት ከተቋሙ ሠራተኞች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ጉዳይ ማስፈጸም የሚችሉበት ሰንሰለት ኖሯቸው ሊሆን የሚችሉበት በርካታ ሁኔታዎች ያጋጥማሉ::

ከዚሁ በተቃራኒ ግርግር ለሌባ ያመቻል እንዲሉ በተቋሞቹ በቂ መረጃ የሚሰጥ አካል ባለመኖሩ የሚፈጠረውን የሰው ምልልስ ለግል ጥቅማቸው ለመጠቀም በማሰብ ብቻ፤ ምንም በተቋሙ ከሚሰሩ አካላት ጋር ግንኙነት ሳይኖራቸው "ጉዳያችሁን እናስጨርስላችሁ፤ ውስጥ ሰው አለን" በማለት ከበርካቶች ብር ለሚቀበሉ አካላት ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል::

የዚህ ሁሉ መነሻ በትክክል መረጃ የሚሰጥ አካል አለመኖር፤ ጉዳዩን የያዘው ባለጉዳይ በተለያዩ አጋጣሚዎች ቢሮ በማይሆንበት ወቅት እንደ ተቋም ተተካክቶ መሥራት የሚቻልበት ሥርዓት አለመኖሩ ነው:: እንኳን ሌላ አገልግሎት ፈልጎ የሄደ የመንግሥት ቢሮዎች ተገልጋይ ይቅርና የተጠቀመበትን አገልግሎት ክፍያ ልክፈል ወይም ለማገኘው አገልግሎት ክፍያ ልክፈል የሚል ተገልጋይ ክፍያ ለመክፈል ደጅ መጥናት ይጠበቅበታል::

ከዚህ ውስጥ የአገልግሎት ክፍያ ልክፈል ብሎ ወደ ኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚያመራ ተገልጋይ ክፍያውን ለመክፈል መብራት አለመኖሩን መስማት የተለመደ ነገር ነው:: በአቅራቢያው የሚገኙ ድርጅቶች የመብራት ችግርን ለመቅረፍ በጄኔሬተር መጠቀምን እንደ አማራጭ መውሰዳቸውን በአካባቢው የተነሱት ጄነሬተሮች በሚያወጡት ድምጽ መረዳት ቢቻልም፤ "ክፍያ ተቀበለኝ" የሚባለው ድርጅት ግን በብዛት ይሄን አማራጭ ሲወስድ አይታይም::

ሠራተኞቹም መብራት "ይመጣል ጠብቁ"፤ ወይም "ሌላ ቅርንጫፍ ሂዱ" የሚል ሃሳብ ከመስጠት በዘለለ "መች ይመጣል?" ሲባሉ "እኛ አናውቅም" የሚል መልስ በመስጠታቸው ምንም ቅሬታ አይሰማቸውም:: መብራት መች እንደሚመጣ ለማወቅ ከተቋሙ ሠራተኛ በላይ ለጉዳዩ የቀረበ ሰው ከወደ የት ይገኛል?

ሌላው በመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚታዩ አገልግሎቶች እንዳይሻሻሉ የሚያደርገው ከኅብረተሰቡ ለሚነሱ ቅሬታዎች ተገቢ ጆሮ ያለውና የሚያርም በቂ አካል አለመኖሩ ይመስላል:: በየቢሮዎቹ "በአገልግሎት አሰጣጣችን ላይ የተሰማዎትን አስተያየት ያስፍሩ" የሚሉ ትልልቅ፣ አቧራ የጠገቡና ተገልጋዩም አገልጋዩም በቅጡ የማያያቸው የመሰሉ አንዱ ጥግ የሚቀመጡ አጀንዳዎች ሃሳብን ለማስፈር ብዙም አይጋብዙም::

ለዚህም ይመስላል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ዘመኑ የማህበራዊ ሚዲያ ነውና በተቋማት አገልግሎት ተጉላልተናል፤ ቅሬታ ተፈጥሮብናል፤ እንዲሁም በደል ደርሶብናል፤ የሚሉ አካላት ቅሬታቸውን ይዘው ወደ ማህበራዊ ሚዲያ ሲመጡ እየተመለከትን ነው:: ታዲያ በዚህ ሂደት ወቀሳ የሚቀርብባቸው አካላት መልስ ካለመስጠት አንስቶ መልስ ሲሰጡም ጉዳዩን ከማጣራት ይልቅ "ስም የማጥፋት ዘመቻ ተከፍቶብናል"ና መሰል ምክንያቶችን በመደርደር ጉዳዩን የማቃለል ዘመቻ ውስጥ ይገባሉ::

መገልገል መብቱ የሆነ ተገልጋይ በተሰጠኝ አገልግሎት ቅሬታ ፈጥሮብኛል ሲል በደፈናው ተቋማችንን አናስነካም ከሚል ድርጊቱን ሳያጣሩ መካድ ቅሬታ ለሚቀርብበት ተቋምም አይጠቅምም:: እንደ አንድ ተራማጅ ተቋም፣ ለድርጅቱ የሚጠቅመው ጊዜ ወስዶ የቀረበው ቅሬታ እውነት ነው ወይስ ሐሰት፤ እውነት ከሆነስ በማንና እንዴት ሊፈጸም ቻለ የሚለውን አረጋግጦ ከነተወሰደው እርምጃ ሲገለጽ ነው:: ያኔ ለተገልጋይ ድርጅቱ ከተባለው ሕገወጥ ድርጊት ጋር ተባባሪ አለመሆኑንና ድርጊቱ በጥቂት ሕገወጦች የሚፈጸም መሆኑን ስለሚያሳይ ከድርጅቱ ጋር ያላቸው ግንኙነት እንዳይቋረጥ ያደርጋል::

ይህ ሳይሆን ሲቀርና ያለምንም ማጣራት ቅሬታ አቅራቢዎቹ ሲፈረጁ በቀጣይ በደል የሚደርስባቸው አካላት ከመፈረጅ ውጪ ምንም አናመጣም በሚል በደላቸውን ለማፈን ይዳረጋሉ::የድርጊቱ ፈጻሚዎችም ሀይ ባይ አካል እንደሌለ ስለሚሰማቸው በሕገወጥ ሥራቸው ለመግፋት ይበረታታሉ:: የደንበኞችን ቅሬታ ሰምቶ ጉዳዩን ከመሰረቱ የማጣራት ሥራ መስራት ፣ ጥፋት ሲፈጸምም የእርምት እርምጃዎች መውሰድ ሊለመድ ይገባል:: ያኔ በቀጣይ ሌሎች ሕገወጦችን ሙሉ በሙሉ ማጥፋት ባይቻል እንኳን መቀነስ ይቻላል::

ዛሬ፣ ዓለም አንድ እየሆነች ነው፤ በዚህ የተነሳም በሀገራችን ለውጭ ሀገር ድርጅቶችና ዜጎች ዝግ ሆነው የቆዩ የሥራ ዘርፎች ከዕለት ወደ ዕለት ክፍት እየሆኑ መምጣታቸው አይቀርም:: ያኔ ብቸኛ የአገልግሎት ሰጪ ሆነው በመቆየታቸው ያላዳበሩት ደንበኛን ያስቀደመ አገልግሎት መስጠት ለኛዎቹ ተቋማት ሲከብዳቸው፤ እድሜ ልካቸውን "ደንበኛ ንጉስ ነው!!!" እያሉ ደንበኛን ያማከለ አገልግሎት ሲሰጡ ለከረሙ የውጭ ተቋማት መልካም እድል ይፈጥርላቸዋል::

የመንግሥት ተቋማት ኅብረተሰቡ ግዴታውን ሳይወጣ ሲቀር እንደሚቀጡት ሁሉ፤ መብቱን የሚጠይቅበት፣ ጊዜውን ሳያባክን የሚፈልገውን አገልግሎት አግኝቶ የሚሄድበት አሠራር ማስፈንን የአገልግሎታቸው አንድና አቢይ አካል ሊያደርጉ ይገባል::

# ነፃ ሃሳብ

# አብሮነት ያጸናው የታሪክ ሰነዳችን

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

የሀገር መሀል አንጓ ሆነው ከትውልድ ትውልድ ከተሻገሩ እውነቶች ውስጥ አብሮነት ቀዳሚውን ቦታ ይይዛል:: ከዚህ ስም ጋር ዳብረንና ተዋህደን ፊተኛ ሀገርና ሕዝብ ስንሆን መነሻችን ወንድማማችነት ነው:: ርቀን በክብርና በሰብዓዊነት ማማ ላይ ስንሰቀል፣ የነፃነትና የፍትሕ ራሶች ስንባል መነሻችን አብሮነት ነው::

አብሮነት ለአንድ ሀገር እንደ ምሰሶ ነው:: ቤት በምሰሶ እንደሚቆም ሀገርም የምትቆመው በሕዝቦቿ የአንድነት መንፈስ ነው:: ይሄ እውነት ስማችን፣ ማንነታችን፣ መገለጫችንና አርማችን ሆኖ ከትላንት ወደዛሬ መጥቷል:: ወደነገም ይቀጥላል::

ኢትዮጵያዊነት ሲነሳ ቀድሞ የሚነሳው አብሮነት ነው:: እንደ ዓድዋ ያሉ በዘመናዊ የጦር መሳሪያና በአካዳሚ የሰለጠኑ ወታደሮችን ያሳፈረ፣ እንደ ሕዳሴ ግድብ ያለ ብዙዎች በአይችሉም ሲስቁብን ችለን የማሳየታችን ዋናው ሚስጢር የህብረት ቡዳኔአችን ነው::

የታሪኮቻችን ደማቅ ገድሎች በወንድማማችነት የጸኑ እንደሆኑ ብዙ ታሪኮችን እንደማስረጃ መጥቀስ እንችላለን:: ተለያይተን ፊተኛ ሆነን አናውቅም:: እንድንለያይ የሚያደርጉ የታሪክ ውርርስም የለንም::

ተደጋግፈንና ተወራርሰን ከእኔ ለእናተ ከእናተ ለእኔ በሆነ የአብሮነት ስብጥር ጎጆ የቀለስን ነን:: እንዴት እና በምን ጥበብ ሀገርና ሕዝብ እንደሆንን ብንጠይቅ ድብልቅ ታሪክ፣ ቅይጥ ማንነትን ከዳበሩ ውርርስ ባሕሎቻችን ጋር እናገኛለን::

የእኔ የአንተ በሌለው የአብሮነት ባህል ውስጥ ተወልደን ስናድግ ተፍገምግመን እንድንቆም ሳይሆን ርቀን እንድንጓዝ ነው:: ኢትዮጵያዊነትን ከአባቶቻችን ስንቀበል በዘርና ብሔር ያልተቧደነ ትውልድ እንድንፈጥር ነው:: እዚም እዛም የምንሰማቸው የብሔር እሳቤዎች ህብረታችንን ከማላለት፣ አንድነታችንን ከማዛል ባለፈ ጥቅም አይሰጡንም::

በክብር ምንጣፍ ላይ ያራመዱን የአባቶቻችን እግሮች፣ በነፃነትና በሰውነት ሚዛን ላይ ያሳረፉን የፊተኞቻችን ልቦች በሀገር ፍቅር ጣይ የወጣባቸው፣ በአብሮነት እውነት የሰነዱ ናቸው:: እንደኔና እንደእናንተ ለማንም በማይበጅ የብኩርና ግፊያ ተጋፍተው የወደቁ ሳይሆኑ ተቃቅፈው የዘለቁ ነበሩ::

ሳንተቃቀፍና ይቅር ሳንባባል የአባቶቻችንን ሀገር አንዋሃዳትም:: ሳንያያዝና ሳንደጋገፍ ህልሞቻችንን ማስቀጠል የማይታሰብ ነው:: በነጣጣይ ትርክት የነጣጠሉን የሀገርና ሕዝብ ባላንጣዎች በእኛ አበሳ ውስኪ እየተጎነጩ እንደሆነ ብናውቅ፣ በአብሮነታችን ውስጥ ጥላቻን ያስቀመጡ የጨዋ እሾሆች የእኛ መነካከስ ለነሱ ልብ አንጠልጣይ ድራማቸው እንደሆነ ብናውቅ በሴረኞች ሴራ ጥንተ ፍቅራችንን ባላጎሸን ነበር:: መነሻው ፍቅርና አብሮነት የሆነ ሕዝብ ከየት ተነስቶ እዚህ እንደደረሰ የሚያውቅ ሕዝብ ነው በትንሾች ሴራ፣ በክፉዎች ተንኮል ክብሩን እንዲጥል ልዕልናው አይፈቅድም:: የለበስነው የክብር ልብስ፣ የተጎናጸፍነው የታሪክ ካባ ህብረ ብሔራዊነት የሸመነው የኢትዮጵያዊነት ሸማ ነው:: ማንም ሊያሳድፈው እና ሊያቆሸሸው አይቻለውም::

እኛ ለኢትዮጵያ ደመራ እንደሚያበራ ችቦ ነን:: በአንድ ተቋጥረንና አብረን ለሀገራችን ብርሃን የሆንን:: እሳቱ ከነኩት ያቃጥላል ከተጠቀሙበት ደግሞ ያበስላል... እኛም እንዲሁ ነን:: ሀገራችን ለእኛ መጠሪያና መድመቂያ ስማችን ናት:: በአንድነትና በወንድማማችነት ከዚም ከዛም ተሰባስበን ነው ሀገራችንን የማገርነው::

አንድነት ኢትዮጵያዊነት የተሠራበት ድርና ማግ ነው:: በታሪክ ድርሳን ላይ ባለታሪክ ሕዝቦች ተብለን የተጠራነው አንድም በህብረታችን አንድም ሰላም ወዳድ ሕዝቦች ስለሆንን ነው:: በጋራ ተጉዘን ያልወጣነው ዳገት፣ ያላሸነፍነው መከራ የለም:: ለዚህ ኢትዮጵያዊነት ጠንስሶት አንድነት የወለደው ታሪካችን ምስክር ነው::

ትላንትን ተያይዘን እንዳለፍን ዛሬም ለገጠሙን ችግሮች መያያዝ ነው የሚያዋጣን:: ችግሮቻችን በልጠውን የመፍትሔ ሃሳብ አጥተን ባለመግባባት ውስጥ የቆምነው በጋራ ከመጓዝ ይልቅ ብቻነትን በመምረጣችን ነው:: የተጀመረው የእርቅና የሰላም ንቅናቄ ከዳር ደርሶ ታሪካችን ከጦርነት ወደ ሰላም ጥንፍ ከረገጠ ብሔርተኝነት ወደ ኢትዮጵያዊነት እንዲሸጋገር መያያዛችን ማስቀጠል አለብን::

**ስለፍቅር ልዩነቶቻችንን በእርቅ እና በዳበረ ሃሳብ መፍታት የመጨረሻው እንደሀገር የመቀጠል አማራጫችን ነው:: አብሮነት በጠንካራ ልቦች ውስጥ የበቀለ በቅሎም የጸደቀ፣ ጸድቆም መቶ ያፈራ ምርጥ ዘር ነው**

ችግሮቻችን በመለያየታችን በኩል የገቡ ናቸው:: እነዚህ ቀዳዳዎች እስካልተደፈኑ ድረስ ሰላም ማምጣትም ሆነ ሰላማዊት ሀገር መፍጠር አይቻልም:: ቀዳዳዎቻችንን ድፍነን የጋራ ሀገር ለመፍጠር ከመለያየት ማጥ ውስጥ ወጥተን በጋራ መጓዝ ለነገ የማንለው ግብራችን ነው::

መለያየት ማቅ ያለብሳል:: መለያየት ሰላምን ነጥቆ የማንግባባባቸውን የንትርክ አጀንዳ ከመስጠት ባለፈ እርባና የለውም:: ከምንም በላይ ሰላም የሚያስፈልገን ሕዝቦች ነን:: ከምንም በላይ ብሔራዊ መግባባት ያስፈልገናል።

የተስፋ ጭላንጭሎች በሁላችንም ላይ ብርሃናቸውን እንዲረጩ ለሰላም ሂደቱ ሃሳብ በማዋጣት የበኩላችንን ልንወጣ ይገባል:: አሁን ባለው ፖለቲካዊም ሆነ ሕዝባዊ ሁኔታ በጎ ትርክቶች ዋጋቸው የላቀ፤ ለእርቅና ለሰላም ሂደቱ ተጨማሪ ጉልበትን የሚሰጥ ነው::

ኢትዮጵያዊነት አንድነት ያሾረው የጋራ ድር ነው:: ሾረን ታሪክ ስንሠራ፣ ሥርዓት ስናበጅ በተዋጣ ሃሳብና ፈትል ነው:: ይሄ የሹረት ድር የጠነከረና የበረታ የሰማኒያ እና የከዛ በላይ መልክና ወዝ፣ ባህልና ወግ ጥምረት ነው:: እንዴትም በምንም ሊበጠስ አይችልም::

በአባቶቻችን የእውነትና የእምነት፣ የፍቅርና የአብሮነት እቅፍ የተገመደ ነው:: የበለጡን ሀገራት አንድነታቸውን አጠንክረው በመዝለቃቸው ነው:: ለዓለም ጥቁሮች የትንሳኤ ጮራ ነን እያልን ለራሳችን መሆን እንኳን እየቻልን አይደለም:: ችግሮቻችን ወደጦርነት እየወሰዱን ነው፣ በጋራ ተግባቦት በኢትዮጵያዊነት የምትጠራ አንድ ሀገር ለመፍጠር እየተንገዳገድን ነው::

ስለፍቅር ልዩነቶቻችንን በእርቅ እና በዳበረ ሃሳብ መፍታት የመጨረሻው እንደሀገር የመቀጠል አማራጫችን ነው:: አብሮነት በጠንካራ ልቦች ውስጥ የበቀለ በቅሎም የጸደቀ፣ ጸድቆም መቶ ያፈራ ምርጥ ዘር ነው:: ቆራጥነት ይጎለናል:: ከምኞት ባለፈ ሰላማችን እንዲመለስ፣ አብሮነታችን እንዲቀጥል የሚጠበቅብንን ዋጋ ስንከፍል አይታይም::

ሀገር የጥቂቶች የሃሳብ ዘር አይደለችም:: ስለአንድነቷና እድገቷ ብዙዎቻችን እናስፈልጋለን:: ቀጣይ በሚኖረው ሀገራዊ ምክክር እያንዳንዳችን አስፈላጊዎች ነን:: በሀገር ግንባታ ሂደት ውስጥ አያስፈልግም፣ አላስፈልግም የሚባል ሃሳብና ሰው የለም::

ከእኛ የሚጠበቀውን ማድረግ ከቻልን በእኛ ኃላፊነት ውስጥ የሚስተካከሉ ብዙ ነገሮች አሉ:: በሁሉም መስክ ላይ እንደ ችግር ከሚነሱ ተግዳሮቶች ውስጥ የመጀመሪያው ራስን የማግለል ሁኔታ ነው:: ራሳችንን አግለን፣ አያገባኝምና አይመለከተኝም እያልን በልካችን የምንፈጥራት ሀገር የለችም::

እኛ ያልተሳተፍንበት፣ ሃሳብ ያላዋጣንበት ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ መስተጋብር፣ ሰላምና አብሮነት የራስን ዐሻራ እንደ አለማሳፈር ተቆጥሮ ሊቆጨን የሚገባ ድርጊት ነው:: በሕይወታችን፣ በኑሯችን ውስጥ ድንቅ ነገር እንዲከሰት ከፈለግን ያለመነጋገር ደካማ ልማዶቻችንን ትተን የሃሳብ ልውውጥ እናድርግ::

ራሳቸውን በከፍታ ላይ ያስቀመጡ ታላላቅ ሀገራት በምንም ሳይሆን በሃሳብ የዳበሩ ናቸው:: የእኛ ማነስ፣ የእኛ ድህነት፣ የእኛ ኋላ መቅረት፣ የእኛ አለመግባባት፣ የእኛ ሰላም ማጣት፣ የእኛ ብሔርተኝነት፣ የእኛ ጎጠኝነት፣ የእኛ መለያየት መነሻው በዳበረ የሃሳብ ልዕልና ውስጥ አለማለፋችን ነው::

ዓለም የዘመናዊነት ካባ የደፋችው፣ ሕዝብ የስልጣኔን በትር የጨበጠው እኮ በሃሳብ በኩል ነው:: ተነጋግረን ካልተግባባንና በአብሮነት ሰላም ካላወረድን ስለሰላም ሌላ ምን መንገድ አለን? በሃሳብ እንዳብር:: ፖለቲካው በሃሳብ ይዳብር፣ ኢኮኖሚው በሃሳብ መሠረቱን ይጣል:: ማህበራዊ ጉርብትናው በሃሳብ ልውውጥ ይታደስ::

ሃሳብ አጥተን ስለፍቅርና ስለሰላም ጦር ብናነሳ፣ ፍቅር አጥተን በዘርና በብሔር ብንቧደን የዚህ ዘመን የመጨረሻው አላዋቂነት ነው:: ሰላምን በጦርነት ለማምጣት በመሞከራችን የብዙዎች መሳቂያ ሆነናል:: መለስ ብለን ራሳችንን መፈተሽ አለብን::

ምን አጣላን ? ከአለመግባባታችን ጀርባ እነማን አሉ? በምን እንዳንግባባ አደረጉን ? ስንል እንጠይቅ:: ከዚህ መጠይቅ በኋላ ዋጋ ባለው ሃሳብና ተራማጅ በሆነ እይታ ለእርቅና ለተግባቦት መቀመጥ ውጤት የሚመጣበት አካሄድ ነው:: የላቀ ሰውነት በላቀ ሃሳብ በኩል የሚታይ ነው::

የላቀ ሀገርና የላቀ መንግሥት በላቀ ሃሳብ በኩል የሚገለጥ ነው:: በእርስ በርስ ፉክክርና በወንድማማቾች ግፊያ እየወደቅንና እየተነሳን መከራችንን ስንበላ የኖርነው በዳበረ ሃሳብ ማጣት ነው:: በሃሳብ እንዳብር፣ በሃሳብ እንበልጽግ፣ በሃሳብ እንሸናነፍ::

ያለፉትን አራት እና አምስት ዓመታት በተደጋጋሚ ጊዜ ስለሃሳብ ተነጋግረንባቸዋል:: በሃሳብ ስንሸናነፍ ግን አንታይም:: እየፈረስን ያለነው በሃሳብ ስላልተገነባን ነው:: ከፊታችን ያለው ብዙሃነት የሚንጸባረቅበት የብሔራዊ የእርቅና የተግባቦት መድረክ መነሻው ሃሳብ እንደሆነ በተደጋጋሚ ጊዜ ተገልጿል:: በዚህ መንገድ ጀምረን ስንጨርስ ብቻ ነው ራሳችንን ነፃ የምናወጣው::

ያጸናው የታሪክ ሰነዳችን በአብሮነት ሃሳብ የዳበረ እንደነበር ነጋሪ አያሻንም:: ኢትዮጵያ ብለን ጀምረን ነው ፋና ወጊ የወጣን:: እኛ ብለን ተነስተን ነው ደማቆች የሆነው:: አሁን እኛነትን ወደእኔነት፣ ኢትዮጵያዊነትን ወደጎጠኝነት ቀይረን ተነጋግረን መግባባት የማንችልበት ራስን ብቻ የማድመጥ ጊዜ ላይ ደርሰናል::

ይሄ ለማንም የማይጠቅም ታሪክ የሚያበላሽ አብሮነትን የሚንድ እጅግ አደገኛ ነገር ነው:: ህልማችን ለውጥና ብልጽግና አብሮነትና ወንድማማችነት ከሆነ ከተዘፈቅንበት ሃሳብ አልባ ምናብ እንውጣ:: ራሳችንን ነፃ እስካላወጣን ድረስ ነፃ አውጪ የለንም:: ነፃ መውጣታችን የሚረጋገጠው ደግሞ ችግሮችን በሰለጠነ መንገድ ፈትቶ አብሮነትን ማስቀጠል ሲቻል ነው::

ታሪክ ከመዘከር ወጥተን ታሪክ ሰሪ እንዲወጣን ከተቧደንበት የብሔር ሽኩቻ ተላቀን ወንድማማችነትን እናዳብር:: ጓዳ ጎድጓዳችን ቢፈተሽ ድብልቅና ውህድ ታሪክ እንጂ የብቻ ታሪክ አይገኝበትም:: ማንም ብቻው ጸንቶ ኢትዮጵያን አላጸናም:: አብረን ተጉዘን ነው ከዚህ የደረስነው ፤ አብረን ለመቀጠልም መያያዝ ያስፈልገናል::

ቀጣዩን ሀገራዊ ርምጃ ከሃሳብ እንጀምር:: ከጥልና ክርክር፣ ከጥላቻና ቂም ጀምረን ብዙ ያፈረስናቸው ታሪኮች አሉን:: የፖለቲካ ምህዳሩ በሃሳብ እንዲታነጽ፣ ማንም ምንም ይሁን በሃሳብ ልቆ መገኘትን የሕይወት መርሁ ማድረግ ይኖርበታል።

ማንም በፍቅር ካልሆነ ማንንም ታግሎ መጣል አይችልም:: የመሳሪያ አፈሙዛችንን መልሰን በፍቅር መቧደንን ቀጣይ መሪ እቅዳችን እናድርግ:: እኛው በእኛ እያለቀስንና እየተወቃቀስን እስከመች እንቀጥላለን ?።

ማንም መጥቶ የደፈረን የለም:: የምንደፋፈረው እርስ በርስ ነው፣ የምንሞተው፣ ጥርስ የምንነካከሰው እርስ በርስ ነው ከዚህ ታሪክ ወጥተን የፍቅር ቤት በመሥራት ከጉስቁልና የምንወጣበት ሁነኛ አቅጣጫ እናጽና::

በእኛ ፍቅር ማጣት ኢትዮጵያ ሀገራችን አይኗ እንባ ካቀረረ ቀይቷል:: እንባዋን ለማበስ ፍቅር መሐረባችን ይሁን:: ተወቃቅሰን ሳይሆን ተሞጋግሰን ሀገር እንሥራ:: ተነቃቅፈን ሳይሆን ተመሰጋግነን በጋራ መኖርን ባህል እናድርግ:: ተራርቀን ሳይሆን ተጠጋግተን፣ ተቀያይመን ሳይሆን ተነፋፍቀን፣ ተናንቀን ሳይሆን ተከባብረን የተስፋ መጻኢ ጊዜያችንን እንውለድ::

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## እምቅ የፈጠራ ችሎታ እየታየበት ያለው አውደ ርዕይ

**ወርቅነሽ ደምሰው**

‹‹በዘመነ ዲጂታል›› በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ያሉ ጀማሪ የሥራ ፈጣሪዎችን (ስታርትአፖችን) ማበረታታት ተገቢ እንደሆነ ይነገራል:: በኢትዮጵያም ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ጀማሪ ሥራ ፈጣሪዎችን የማበረታታቱ ሥራ ተጠናክሮ ቀጥሏል:: ለዚህም ብዙ ማሳያዎችን ማንሳት ይቻላል::

ከማሳያዎቹ መካከልም ከሰሞኑ በሳይንስ ሙዚየም እየተካሄደ ያለው ‹‹የጀማሪ የሥራ ፈጣሪዎችን ስታርትአፖች አውደ ርዕይ›› አንዱ ነው:: አውደ ርዕዩ ከመጋቢት 30 ጀምሮ እስከ ሚያዚያ 28 ድረስ የሚቆይ ሲሆን በአውደ ርዕዩ በርካታ ጀማሪ የፈጠራ ሃሳብ ያላቸው አካላት የሚሳተፉበትና የፈጠራ አቅማቸውን የሚያሳዩበት እንደሚሆን ይታመናል::

የዝግጅት ክፍላችን በአውደ ርዕዩ ተገኝቶ በጀማሪ የሥራ ፈጣሪዎቹ የቀረቡ የፈጠራ ሃሳቦችን በመቃኘት ያዘጋጀውን ይዞ ቀርቧል:: በአውደ ርዕዩ ሥራቸውን ካቀረቡ ጀማሪ የሥራ ፈጣሪዎች መካከል ዶክተር ፍቃዱ ድሪባ አንዱ ነው።

ዶክተር ፍቃዱ አውቶማቲክ የኤሌክትሪክ ኃይል መቆጣጠሪያ መሳሪያ/አውቶማቲክ ኤሌክትሪክ ፓወር ሬጉሌሽን ዲቫይስ /ፈጠራ ባለቤት ነው። የዚህ ፈጠራ ጠቀሜታ እንደ ሀገር ላለው የመብራት ኃይል መቆራረጥ ችግር መፍትሔ የሚያመጣ ነው::

አሁን ላይ የኤሌክትሪክ ኃይል ከመብራት ኃይል እያንዳንዱ ተጠቃሚ ጋር እስኪደርስ 35 በመቶ ያህል የኃይል መቀነስ እየተከሰተ መሆኑን መረጃዎች እንደሚያመላክቱ የሚናገረው ዶክተር ፍቃዱ፤ በኢንዱስትሪዎች እንዲሁ የኤሌክትሪክ ኃይል መቀነስ ሆነ ተያይዘው የሚነሱ ችግሮች መኖራቸውን ጠቅሶ፤ ይህ የፈጠራ ቴክኖሎጂ ለችግሮቹ መፍትሔ በማምጣት የኃይል መቀነስንም ሆነ በየጊዜው የሚያጋጥመውን የመብራት ኃይል መቆራረጥ ለማስቀረት ያስችላል ይላል።

የአውቶማቲክ የኤሌክትሪክ ኃይል መቆጣጠሪያ መሳሪያው ሦስት ነገሮችን መሥራት የሚያስችል ሲሆን፤ የኤሌክትሪክ ኃይል መቆጣጠር፣ የቮልቴጅ መጠንን መጨመር እና የኃይል ፍጆታ በመቀነስ የሥርዓት አቅምን እንደሚጨምር ያመላክታል።

ይህን የፈጠራ ሥራ የጀመረው 2009 ዓ.ም አካባቢ እንደነበር የሚያነሳው ዶክተር ፍቃዱ፤ ነገር ግን በመሀል አቋርጦ ወደሌላ ሥራዎች ማዘንበሉን ነው የገለጸው:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ለጀማሪ የፈጠራ ሥራዎች የተሰጠው ትኩረት ሥራውን አጠናክሮ እንዲቀጥል ምክንያት እንደሆነም አልሸሸገም::

የፈጠራ ሥራው በአእምሯዊ ንብረት ጥበቃ ጽሕፈት ቤት ተመዝግቦ የፈጠራ ባለቤትነት መብት ተሰጥቶታል:: በተጨማሪም በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አማካኝነት የሶፍት ዌር ፕሮግራም እና ሰፊ የቴክኖሎጂ ሥራ እንዲኖረው ተደርጓል።

ዶክተር ፍቃዱ፤ አሁን ላይ ጃንግል ፓውር ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ የተሰኘ ድርጅት በመመሥረት ቴክኖሎጂውን ለማምረት በሂደት ላይ እንደሚገኝ ይናገራል:: ቴክኖሎጂው በስታርትአፕ በሚያገኘው የፋይናንስ ድጋፍ በቅርቡ ወደ ማምረት ሥራ እንደሚገባ ይገልጻል:: ከዚህ በተጨማሪም ሌሎች የፋይናንስ ድጋፍ ለሚያደርጉ አካላት ጥናት ተደርጎ ቢዝነስ እቅድ ተነድፎለት አስፈላጊውን ድጋፍ እያደረጉ መሆኑን ያመላክታል::

‹‹ቴክኖሎጂው ከ20 ዓመት በላይ ካለ ምንም ጥገና ሊያገለግል ይችላል:: ይህ የፈጠራ ውጤት ተግባር ላይ ሲውል ሁሉንም ሰው የሚጠቅም ነው:: ለምሳሌ ቴክኖሎጂውን የሚጠቀመው አንድ ፋብሪካ ቢሆን ፋብሪካው ይህን ቴክኖሎጂ ሲጠቀም የኤሌክትሪክ ኃይል ፍጆታውን ይቀንስለታል። በመሆኑንም ቴክኖሎጂውን ሲጠቀም የቴክኖሎጂውን የገዛበትን ዋጋ አሁን ላይ በኤሌክትሪክ ኃይል ብክነት የሚከፈለውን ቅጣት ከዓመት ባነሰ ጊዜ ሊመልስ ይችላል›› በማለት አስረድቷል::




‹‹ቴክኖሎጂ በሀገራችን የመጀመሪያ የፈጠራ ሥራ ነው›› የሚለው ዶክተር ፍቃዱ፤ ኢንዱስትሪዎች በአዲሱ የፈጠራ ቴክኖሎጂ ሲጠቀሙ ቀደም ሲል እየባከነ ያለውን ኃይል መቆጠብ ስለሚችሉ ይህ የሚቆጥቡትን ኃይል ለሌላ ማሽን ማዋል እንደሚችሉ ያስረዳል::

‹‹ለፈጠራ ሥራ የሚያስፈልገው ኤሌክትሪክ ዲቪይስ ከውጭ ሀገር የሚመጣ ሲሆን፤ ፒሲቢ ቦርዱን እዚሁ ዲዛይን አድርጎ ለመሥራት ማሽኑ በመኖሩ በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ተፈቅዶልኛል›› የሚለው ዶክተር ፍቃዱ፤ ድርጅቱ ሲቋቋም ‹‹ፒሲቢ ቦርዱን›› እና ‹‹ሰርፌስ ቦርድ›› የሚያመርት ማሽን ከውጭ ማስገባት ከተቻለ ሌላውን ሥራ በሙሉ ሀገር ውስጥ እንደሚሠራ ይናገራል::

ቴክኖሎጂ ተግባራዊ ሲደረግና ሥራ ሲጀምር በመጀመሪያ ዙር 500 ዜጎች የሥራ እድል ይፈጥራል:: ወደፊት ከአምስት ዓመታት በኋላ ደግሞ ከሀገር ውስጥ ፍጆታ ተርፎ ወደ አፍሪካ ሀገራት ኤክስፖርት ለማድረግ እቅድ እንዳለው ያመላክታል:: ይህን ቴክኖሎጂ ሀገር ውስጥ በማሳደግ ለሀገር ጥቅም ላይ እንዲውል በማድረግ ትውልድ የሚጠቀምበት እንዲሆን በሀገር አቅም ሠርቶ ማሳደግ ይቻላል የሚል ፅኑ አቋም ይዞ እየሠራ እንደሆነ ገልጿል::

‹‹ይህ ፈጠራ በስታርትአፕ ደረጃ መሥራት ከጀመርኩ ሦስት ዓመታት ያህል ሆኖኛል። ነገር ግን በጊዜው የስታርትአፕ ሃሳብ በደንብ ስላልታወቀ የሚደግፈኝ አካል ባለመኖሩ እስካሁን እንድቆይ አስገድዶኛል›› ያለው ዶክተር፤ አሁን ላይ እስካሁን ማነቆ የሆኑ ችግሮች ተቀርፈው ሕጎች እየጸደቁ ሲሆን ጀማሪ የሥራ ፈጣሪዎች ለሀገር ትልቅ ሥራን የሚሰሩበት ሰፊ ምህዳር እየተፈጠረላቸው ስለሆነ ሊጠቀሙበት ይገባል በማለት መልዕክቱን አስተላልፏል::

ወጣት ሳሙኤል ጌትነት እና ጓደኞቹ ከተረፈ ምርቶች የሚያመረቷቸውን የተለያዩ ምርቶች ይዘው ቀርበዋል። የሳር፣ የወረቀት፣ የእምቦጭ አረም እና የእንሰት የተረፈ ምርት ተጠቅመው ምርቶችን ያመርታሉ::

እነ ሳሙኤል አላስፈላጊ ከሆኑ እና ተቃጥለው የአካባቢ አየር ንብረት የሚበክሉ ተረፈ ምርቶች ተጠቅመው መልሶ ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ ሁለት ዓይነት ምርቶችን አመርተዋል። አንደኛው የተለያዩ ቁሳቁሶችን ለመያዝ የሚያገለግለ ዘንቢል / ፓኬጂንግ/ ሲሆን፤ ሁለተኛው የኬክ ፕሌት ነው::

ሳሙኤል እንደሚለው፤ የዘንቢል ምርቶቹ በሀገራችን ለተለያዩ ዓይነት የእቃ መያዣዎች የሚያገለግሉና ፌስታሎችን የሚተኩ ናቸው:: እነዚህ ፓኬጆች ፌስታልን መተካት ብቻ ሳይሆን የአፈርን ለምነት የማይጎዱ ከአካባቢው አየር ንብረት ጋር ተስማሚም ናቸው:: በጣም ጠንካራ እና በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ረጅም ጊዜ የሚቆዩም ናቸው::

አሁን ላይ በሀገራችን ያሉት የፌስታል ምርቶች ከፍተኛ የሆነ የገበያ ፍላጎት ያላቸው መሆኑን ጠቅሶ፤ በወር ከስድስት እስከ ስምንት መቶ ሺ የሚሆን የፌስታል ምርት እንደሚፈለግ ያመላክታል:: በመሆኑም ይህን ፌስታል በዘንቢል ምርት በመተካት ያለውን ሰፊ የሆነ የገበያ ፍላጎት አላማ ያደረገ ሥራ መሥራት እንደቻሉ ነው ወጣት ሳሙኤል የሚናገረው::

ሁለተኛው ምርት የኬክ ፕሌት ሲሆን፤ ይህም ኬክን ለመሥራት አስፈላጊ የሆነ የኬክ ማስቀመጫ ነው:: በኬክ ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልጉ ሰዎች ከሚያነሱት ችግር አንዱ የኬክ ፕሌት በሀገር ውስጥ አለመኖር ነው ያለው ሳሙኤል፤ በሀገር ውስጥ የሚያመርቱትም ቢሆን፤ ይህ የኬክ ፕሌት ለማምረት የሚጠቀሙበት ጥሬ እቃ ከውጭ የሚያስገቡ በመሆኑ በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ ይቸገራሉ:: ይህ የፈጠራ ሥራ ግን በኬክ ዙሪያ ሲነሱ የነበሩ ችግሮችን የሚቀርፍና ለብዙ ሰዎች የሥራ እድል የሚፈጥር ነው ይላል::

አሁን ላይ ከውጭ የሚመጣው የአንድ የኬክ ፕሌት ዋጋ 120 ብር ሲሆን፤ የእነርሱ ምርት በ45 ብር ለገበያ እየቀረቡ ይገኛል:: ስለዚህ ወደ ኬክ ማምረት ሥራ ለመሰማራት ለሚፈልጉ አካላት በቅርበት ሊያገኙት እና ወጪም ሊቀንስላቸው እንደሚችል ይናገራል::

አሁን ላይ ለሰባት ሰዎች የሥራ እድል መፍጠር የቻሉ ሲሆን፤ በቀጣይም በርካታ የሥራ እድል መፍጠር የሚያስችላቸው እንደሆነ አመላክቷል:: በቀጣይም አስፈላጊ የሆኑ ማሽኖችን አሟልቶ በሙሉ አቅም ማምረት ሲቻል ጥራት ላይ የሚነሳውን ችግር መፍታት ይቻላል:: ጥራት ያለው ተወዳዳሪ የሆነ ምርቶችን በማምረት ከውጭ የሚገቡት በሀገር ውስጥ ምርት መተካት ብቻ ሳይሆን ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ ጭምር የውጭ ምንዛሪ ማምጣት ይቻላል ብሏል::

ይህን የፈጠራ ሃሳብ ለመሥራት ያነሳሳቸው በአካባቢያቸው ላይ የሚያዩት የተጣሉ ቆሻሻዎች እንደሆኑ የሚናገረው ወጣት ሳሙኤል፤ ችግሩን ለመቅረፍ ደግሞ የሚያስችል የመፍትሔ ሃሳብ ለማምጣት ባደረጉት ጥረት የፈጠራ ሃሳቡ መጠንሰሱን ይናገራል:: ወደዚህ ሥራ ከገቡ ዓመት ከሦስት ወራት ገደማ የሆናቸው ሲሆን አሁን ምርቶቻቸውን እያመረቱ ለገበያ እያቀረቡ ይገኛሉ:: በተለይ የኬክ ፕሌት በጎንደር እና በባህር ዳር ከተማ በጥሩ ሁኔታ እየተሸጠ መሆኑን ይናገራል::

አሁን ላይ በወር ሶስት ኩንታል (300 ኪሎ) ያህል የኬክ ፕሌት እያመረቱ ሲሆን፤ የገበያ ፍላጎቱ ግን ከዚህም በላይ እንደሆነ ነው ያመላከተው:: አሁን ላይ እየተመረተበት ያለው ማሽን በራሳቸው የተሠራና ማኑዋል ማሽኖች ሲሆን፤ እነዚህ ማሽኖች ዘመናዊ ዲጂታል ማሽን መቀየር ከተቻለ በወር የሚመረተው ምርት መጠን በአንድ ቀን ማምረት እንደሚቻል ያስረዳል::

ሳሙኤል እንደሚለው፤ የዘንቢል ምርቶችን እንዲሁ በባህር ዳር እና ጎንደር ከተማ በተለይም ለልብስ ቤቶች፣ ለአትክልት ቤቶች እያቀረቡ ይገኛሉ:: ዘንቢሎቹ ሦስት ዓይነት መጠን ያላቸው ሲሆን፤ ዋጋቸውም እንደየመጠናቸው የሚለያይና አራት፣ ሰባትና አስር ብር ድረስ ነው:: ዘንቢሎቹ አሁን ላይ ሸማቹን እያማረሩ ወዲያውኑ የሚቀደዱ ፌስታሎችን በመተካት ሸማቱ ረጅም ጊዜ ሊገለገልባቸው የሚችሉ ናቸው::

አሁን ላይ የተለያዩ ስልጠናዎች እያገኙ መሆናቸውን የሚናገረው ሳሙኤል፤ እነዚህ ምርቶች በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ከትንሽ ነገር ላይ ተነስተው መሥራት ከቻሉ ዲጂታል ማሽኖች ቢያገኙ ደግሞ ጥራቱን ለመጨመር እና የበለጠ ምርቶቻቸው በማሻሻል ጥራት ያላቸው ተወዳዳሪ ምርቶችን ማምረት እንደሚችሉ ይገልጻል::

ይህ የፈጠራ ሥራ በማሳደግ ምርቶቻቸው ከሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ተደራሽ ማድረግ ፍላጎት ያላቸው መሆኑን ጠቅሶ፤ በቀጣይም የሀገር ውስጥ ፍጆታን ማሟላት ከተቻለ ወደ ውጭም ኤክስፖርት የማድረግ እቅድ እንዳላቸው አመላክቷል::

ሌላኛው ፈጠራ ሥራ የአፍሮ ሪድ የሞባይል የተሰኘ የሞባይል መተግበሪያ ነው:: የአፍሮ ሪድ የሞባይል መተግበሪያ የማስታወቂያና የማርኬቲንግ ባለሙያ ወጣት ናርዶስ ዓለማየሁ እንደምትለው፤ ይህ መተግበሪያ በእ.ኤ.አ 2020 በአራት ኢትዮጵያውያን የተቋቋመ እንደሆነ ትናገራለች:: የዚህ መተግበሪያ ጠቀሜታ ንባብ ላይ የሚታየውን ችግር ለመቅረፍም ያለመ ነው::

አሁን ላይ ባለው የወረቀት ዋጋ ንረት የተነሳ ደራሲያን ሥራቸውን ለማሳተም የማይችሉበት እና አንባቢውም እንዲሁ የታተመውን መጽሐፍ እንኳን በተተመነለት ዋጋ ለመግዛት የማይችልበት ሁኔታ ላይ ደርሷል:: የምትለው ናርዶስ፤ የሁለቱን ችግር ባገናዘበ ሁኔታ ተጠቃሚ የሚያደርግ መተግበሪያ ለማዘጋጀት በማለም ወደዚህ ሥራ እንደገቡ ትናገራለች::

ናርዶስ እንደምትለው፤ መተግበሪያው መጻሕፍት በዲጂታል ለማንበብ ምቹ በሆነ መልኩ ተዘጋጅተው ይቀርባሉ:: በተጨማሪም ከሥራ ጋር ለማይመቻቸው፣ ማየት ለተሳናቸው እና ማዳመጥ ለሚቀናቸው ሰዎችም እንዲሁ የሚፈልጋቸውን መጻሕፍቶች በኦዲዮ ቅጂ ይቀርባል:: በኮፒ ራይት አንጻር መጽሐፉን በኮፒ እንዳይወሰድ የሚያደርግ አሠራር የተዘረጋለት ሲሆን፤ መጽሐፉን የገዛው ሰው በየትኛው መንገድ ለሌላ ሰው ማጋራት እንዳይችል ተደርጓል::

ከዚህ በተጨማሪ መተግበሪያው ደራሲው ምን ያህል መጽሐፍ እንደተሸጠለት ለማወቅ የሚያስችለው አሠራር ያለው በመሆኑ ደራሲ የተሸጠለትን መጽሐፍ አስቀድሞ ማወቅ እንዲችል ተደርጎ የተዘጋጀ መሆኑን ናርዶስ ትገልጻለች::

መጻሕፍት ወደ መተግበሪያው የሚገቡትም በደራሲው ፈቃደኛነት ላይ ተመስርቶ ነው የምትለው ናርዶስ፤ አሁን ላይ ከ200 በላይ ነባር እና አዳዲስ ደራሲዎች በህብረት በመሥራት ከ500 በላይ መጻሕፍትን ተደራሽ ማድረግ ችለዋል ነው ያለችው::

‹‹የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች በማስተዋወቅ የንባብ ባህል ለማዳበር እየሠራን በመሆኑ እስካሁን ከ11ሺ በላይ ሰዎች መጻሕፍት መግዛት የቻሉበት ሁኔታ አለ›› የምትለው ናርዶስ፤ ህብረተሰቡን ወደ ዲጂታል በማምጣት መጻሕፍትን በዲጂታል ሲስተም ገዝተው እንዲጠቀሙ ለማድረግ የማስታወቂያ ሥራዎችን እየሠሩ መሆኑን አመላክታለች::

‹‹አንድ ደራሲ መጽሐፉ ወደ መተግበሪያ እንዲገባ ለማድረግ የሚያወጣው ምን ዓይነት ወጪ የለም:: መጽሐፉ መተግበሪያው ላይ ከተጫነና ከተሸጠ በኋላ ግን የደራሲው ድርሻ 50 በመቶ ያህል ሲሆን የተቀረው 50 በመቶ የድርጅቱ ድርሻ ይሆናል›› ትላለች::

አሁን ላይ ደራሲው ሆነ አንባቢዎች መጻሕፍትን በዲጅታል በዚህ መንገድ ማግኘት በመቻላቸው ደስተኛ መሆናቸው አስተያየት እየሰጣቸው መሆኑን ጠቅሳ፤ በቀጣይ ተደራሽነታቸውን በማስፋት የንባብ ባሕልን ለማዳበር እንደሚሠሩ አመላክታለች::

# ወቅታዊ ትንታኔ

# ስታርትአፖች - ለሀገራዊ ምጣኔ ሀብት ዕድገት

**ስምስም መንግሥቱ**

ወደ ገበያ ሊወጣ የሚችል የተለያየ የፈጠራ ሃሳብና ችግር ፈቺ የሥራ እቅድ ይዘው ነገር ግን አሳሪ በሆኑ ሕጎች፣ ትኩረት ባለማግኘታቸውና በተለያዩ ምክንያቶች የፈጠራ ሃሳባቸው መክኖ የሚቀርባቸው ሥራ ፈጣሪዎች ብዙ ናቸው።

የመፍጠር ክህሎት (ታለንት) ያላቸው ነገር ግን ክህሎታቸውን ወይንም ሃሳባቸውን ወደ ተግባር ለመለወጥ እክል ያጋጠማቸው በርካታ ወጣቶች አሉ። በዋነኝነትም ለሥራ መነሻ የሚሆን የገንዘብ አቅም አለመኖር፣ የሥራ ቦታ አለማግኘት፣ የሚደግፋቸው ሕግ አለመኖርና የመንግሥት ትኩረት ማነስ በዋናኝነት ከሚገጥሟቸው ችግሮች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው።

እነዚህን ተግዳሮቶች ተቋቁመው ውጤታማ ከሆኑ ከጥቂት የፈጠራ ሃሳብ አፍላቂዎችና ችግር ፈቺ የሥራ እቅዳቸውን ከተገበሩት በስተቀር ብዙ የፈጠራ ሃሳቦችና እቅዶች ባክነው የሚቀሩ ናቸው።

ለገበያ ሊውሉ የሚችሉ የፈጠራ ሃሳቦችና ችግር ፈቺ የሥራ እቅድ ያላቸው ስታርትአፕ ኢንተርፕሪነሮች (ጀማሪ ሥራ ፈጣሪዎች)፤ በአጭር ጊዜ ፈጠራ የታከለበት፣ በአጭር ጊዜ ደግሞ በርካታ ሀብት ለማመንጨት የሚችሉ ጀማሪ ቢዝነሶች ተብለው ይገለጻሉ። በዚህ መልኩ የሚገለጹት ኢንተርፕራይዞች አብዛኞቹ በወጣትነት እድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ እንደሆኑ ይገመታል።

ሃሳባቸውና የሥራ እቅዳቸው ወደተግባር ቢሸጋገር አፍላ በሆነው እድሜያቸው ለሀገር ብዙ የሚጠቅም ነገር ሊያበረክቱ እንደሚችሉ ይታሰባል። ለዚህም ይመስላል መንግሥት ስታርትአፕ ኢንተርፕሪነሮችን በሚችለው ሁሉ በመደገፍ የሚበረታቱበትን ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር እንቅስቃሴውን ያጠናከረው። አሳሪ የሆኑ የሕግ ማዕቀፍ ማሻሻያ ርምጃ በመውሰድና የተለያዩ ድጋፎችንም በማድረግ መንግሥት ዝግጁነቱን በተግባር አሳይቷል።

መንግሥት ስታርትአፕ ኢንተርፕሪነሮችን ለማገዝ ያለው ዝግጁነትና ቁርጠኝነት፣ እንዲሁም ሥራ ፈጣሪዎች መበረታታቸው በሀገር የኢኮኖሚ እድገት ላይ ሊኖረው የሚችለው ፋይዳ እንዴት ይገለጻል? ስንል ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ባለሙያዎችና ኃላፊዎች አነጋግረናል።

በጉዳዩ ላይ፤ የምጣኔ ሀብት ባለሙያው የሆኑት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርኽተስፋ እንደሚናገሩት ፤ ስታርት አፕ የሀገር ኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ሞተር ነው።

በሌላው ሀገር ኡበር በሚል የሚታወቁና በኢትዮጵያ ደግሞ ራይድ የሚባሉ የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች በቢሊየን ዶላር የሚቆጠር ሀብት ማፍራት የቻሉ ስታርትአፖች ናቸው።

እንደ ምጣኔ ሀብት ባለሙያው ማብራሪያ፤ ሀገራችን ውስጥም ወጣቶች የፈጠራ ችሎታቸውን በመጠቀም ትልቅ ኩባንያ መፍጠር ይችላሉ። ለምሳሌ ናይጄሪያ፣ ኬኒያ፣ ሴኔጋል፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ስታርትአፕ የሚባሉ ከውጭ ሀገር በሚሊዮን ዶላር የሚቆጠር ካፒታል መሳብ ችለዋል። በአፍሪካ ውስጥ በቢሎን ዶላር የሚቆጠር ሀብት ያሰባሰቡ ስታርትአፖች አሉ።

ያደጉ የዓለም ሀገራት እንደነ ሰሜን አሜሪካ፣ ደቡብ አሜሪካ፣ እስያ ያሉ ሀገራት በአሁኑ ጊዜ የተጨናነቀ በመሆኑ በርከት ያለ ኢንቨስትመንት እየመጣ ያለው ለአፍሪካ ስታርትአፖች ነው። ይሄ ለአፍሪካ ሀገራት ትልቅ ጥቅም አለው።

ስታርትአፕስ ብዙ ጊዜ የሚገናኙት ከካፒታል ገበያ ጋር ነው። ሃሳባቸውንና የሚያቅዱትን ነገር በካፒታል ገበያው ላይ ትንሽ ካንቀሳቀሱ በኋላ በካፒታል ገበያው ላይ አክሲዮን በመሸጥ ከፍተኛ ገንዘብ ያገኛሉ። ሰሜን አሜሪካንና ቻይና ያሉ ብዙ ስታርትአፕስ በካፒታል ገበያው ላይ ነው እራሳቸውን በማሳደግ ምሳሌ የሚሆኑ ናቸው።

ዶክተር ቆስጠንጢኖስ የኢትዮጵያ መንግሥትም ይህን ሁሉ ከግምት ውስጥ አስገብቶና የሀገርን ተጠቃሚነት አስቀድሞ ለዚህ ጉዳይ ትኩረት መስጠቱ ያስመሰግነዋል ብለዋል።

እርሳቸው እንደሚሉት፤ ስታርትአፕስ ካፒታል የላቸውም፤ ባንኮችም ብድር ለመስጠት መያዣ (ኮላተራል) ይጠይቃሉ። ወይንም ደግሞ በቅድሚያ 30 በመቶ ወይንም 40 በመቶ እንዲያሲዙ የሚጠየቁበት አሰራር ነው ያለው። በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አንድ ስታርትአፕ ቢሮ መክፈት፣ አድራሻ ማሳወቅ አለበት። የሥራ ፈቃድ የመሳሰሉት ማነቆዎች አሉ። ስታርትአፖች



ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርኽተስፋ

ግን በዚህ ሁሉ አስጨናቂ ሁኔታ አልፈው መሄድ የሚያስችል አቅም የላቸውም። ስለዚህም መንግሥት እነዚህም ማነቆዎች እየፈታ መምጣቱ ስታርትአፖች በቀላሉ ፍሬ እንዲያፈሩ በር የሚከፍት ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በሌላም በኩል በኢትዮጵያ የውጭ ባንኮች መግባት ለስታርትአፖች ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ባለሙያው ይናገራሉ። ‹‹የውጭ ባንኮች ኢትዮጵያ ውስጥ እንደሚገቡ ከዚህ ቀደም በመንግሥት ተገልጿል።

እነዚህ ባንኮች የፈጠራ ችሎታ ያላቸውን ወጣቶች ያበረታታሉ ተብሎ ይጠበቃል። ባንኮቹ በመያዣነት የሚጠይቁት ፕሮጀክታቸውን ነው። ወጣቶቹ አዲስ ኩባንያ በሚጀምሩበት ጊዜ የወሰዱትን ብድር ምን ላይ አዋሉት የሚሉ መስፈርቶችን አስቀምጠው ነው እየተቆጣጠሯቸው ገንዘብ የሚሰጧቸው። ስታርትአፕስ በዚህ መንገድ ከታገዙ ለሀገር ጥቅም የሚሰጡ ናቸው›› ሲሉም አስረድተዋል።

በንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ መደበኛ ያልሆኑ፣ የጎዳና ላይ ነጋዴዎች ተብለው በደንብ አስከባሪዎች የሚሳደዱት የፈጠራ ሥራ ስላላቸው እንደሆነና እነዚህ የጎዳና ላይ ነጋዴዎች አድገው ነገ ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ሊሆኑ እንደሚችሉም ገልጸዋል።

መንግሥት በስታርትአፖች ላይ ስጋት ሊያድርበት አይገባም የሚሉት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፤ ስታርትአፕስ ከሥራ አጥነት ወደ ሠራተኛነት፣ ብሎም ወደ ሠራተኛ ቀጣሪነት የሚሸጋገሩ እንደሆኑ፣ የመንግሥትን ሥራ የመፍጠር ጫና በከፍተኛ ሁኔታ የሚያቃልሉ መሆናቸውን አመልክተዋል። መንግሥት የሚያሠራ ፖሊሲ ማውጣትና ሌሎችንም ምቹ ሁኔታ መፍጠር ነው የሚጠበቅበት ሲሉ ገልጸዋል። የጉምሩክ አሠራሮችን በቀበሌና በወረዳ ያሉ የአሠራር ማነቆዎች እንዲፈቱና የተቀላጠፈ አገልግሎት መኖር እንዳለባቸውም ይጠቅሳሉ።

የውጭ ባንኮች በሀገር ውስጥ ሥራ ጀምረው ለስታርትአፖች የሚሆን መዋዕለ ነዋይ እስኪያመቻቹ ድረስ መንግሥት ምቹ ሁኔታ መፍጠር ይጠበቅበታል የሚሉት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፤ ‹‹ጊዜውን በትክክል ባልገልጸውም ከዛሬ አስር ዓመት በፊት ይመስለኛል መንግሥት ወደ 10 ቢሊየን ብር በመመደብ ወጣቶች በተለያየ የሥራ መስክ ላይ እንዲሰማሩ ሁኔታዎችን አመቻችቶ ነበር። እንዲህ ያሉ ነገሮች ያስፈልጋሉ። ይህን በልማት ባንክ ወይንም በንግድ ባንክ በኩል ማመቻቸት ይቻላል። የኢንቨስትመንት ባንኮች ከመጡ በኋላ ግን ስታርትአፖች እራሳቸው ሃሳባቸውን እያቀረቡ በቀላሉ ብድር የሚያገኙበት ሁኔታ ይፈጠራል›› በማለት የመንግሥት ዋነኛ ተግባር የተቀላጠፈ አሠራር ሥርዓት መዘርጋት መሆኑን አስምረውበታል።

እንደ ዶክተር ቆስጠንጢኖስ ገለጻ፤ ሃሳብ ሁሉ ስታርትአፕ መሆን ይችላል። ለምሳሌ ወጣቶች ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር የተለያዩ ነገሮችን መሥራት የሚያስችላቸው ዕድሎች አሉ። እንደ ሕንድ ናይጄሪያ ሴኔጋል ያሉ ሀገሮች በተንቀሳቃሽ ስልካቸው በግብርና ሥራ ላይ ለተሰማሩ የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ እያገዟቸው ነው። ማዳበሪያን ጨምሮ የተለያዩ የግብርና ግብዓቶችን መግዛት ያስችላቸዋል። እንዲህ ያለው ሃሳብ ትንንሽ ሊመስል ይችላል። ነገር ግን ጥቅሙ ሰፊ ነው። ቴክኖሎጂውን ተጠቅመው ለአርሶ አደሩ ሁኔታዎችን የሚያመቻቹ ጥቅሙ ለሀገርም ጭምር መሆኑን ይናገራሉ።

ዶክተር ቆስጠንጢኖስ የውጭ ሀገራትን ተሞክሮ አስመልክተው እንደተናገሩትም ‹‹ዛሬ ስመጥር የሆኑት እነ አፕል፣ ማይክሮሶፍት በቤተሰባቸው የመኪና ጋራዥ ውስጥ በአነስተኛ ሥራ ተጀምረው ነው በዓለም ውስጥ በሀብት መጠናቸው በከፍተኛ ደረጃ ሊጠሩ የበቁት።

በኢትዮጵያም አስፈላጊውን ነገር ማመቻቸት ከተቻለ እንዲህ ያለውን እድል ማምጣት የማይቻልበት ሁኔታ አይኖርም። መንግሥት ሕግ ከማስከበር፣ መሠረተ ልማትን ከማሟላት አልፎ የግሉ ዘርፍ ሊሠራቸው በሚችላቸው ነገር ውስጥ መግባት አይጠበቅበትም። እንደ ሀገር ከሚሰበሰብ ታክስ ገቢን ለማሳደግ የግሉን ዘርፍ ማበረታታት ያስፈልጋል።›› ሲሉ ሃሳባቸውን ደምድመዋል።

የሥራ እና ክህሎት ሚኒስትር ወይዘሮ ሙፈሪያት ካሚል በበኩላቸው፤ የመንግሥት እገዛ ከንግግር ባለፈ በተለያየ መንገድ የሚገለጽ መሆኑን ይናገራሉ።

የመንግሥት ቁርጠኝነት በተግባር የተረጋገጠ መሆኑንን በመጥቀስ፤ የተጀመረውን ሥራ ለማሳለጥ የሚችሉ ተቋማትን በማደራጀት፣ በአሠራር፣ በፖሊሲ፣ በሕግ በፋይናንስ ድጋፍ መሥሪያና መሸጫ ቦታዎችን ምቹ በማድረግና በሌሎችም ድጋፎችን እያደረገ ባለው ሥራ ይገለፃል ብለዋል።

አዳዲስ ፖሊሲዎችን በማውጣት የወሰደው ርምጃ ሌላው መገለጫ መሆኑን የተናገሩት ሚኒስትሯ ለአብነት ጥቃቅን፣ አነስተኛ፣ መካከለኛ የሚባሉ ኢንዱስትሪዎችና ከፍተኛ የማደግ አቅም ያላቸውን ኢንዱስትሪዎች ጨምሮ ሁሉንም ሊደግፍ የሚችል ፖሊሲ መውጣቱንም ተናግረዋል። ፖሊሲው ስታርትር አፖችን ሊደግፉ የሚችሉ ወደ ዘጠኝ ገደማ የሚሆኑ ምሶሶዎችን የያዘ መሆኑንም አንስተዋል። ፖሊሲውን ተከትሎም አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ይወጣሉ ብለዋል።

እገዛው ሥራን አስቸጋሪ በሆነ መንገድ መፍጠር ሳይሆን፤ በተሻለና በተሳለጠ መንገድ መፍጠር የሚቻልበትን እድል የሚሰጥ እንደሆነ የጠቀሱት ወይዘሮ ሙፈሪያት፤ የስታርትአፕ ፖሊሲውም እንዲሁ ከሕግና ከፖሊሲ አኳያ፣ እንዲሁም ሌሎች ከአሠራር ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል መሆኑን አስረድተዋል።

ፖሊሲው ወደ ዘጠኝ ገደማ የሚሆኑ ትላልቅ የፖሊሲ ሃሳቦችን የፋይናንስ ጉዳዮችን ጨምሮ የክህሎት ልማት ሥራዎችን ያካተተ የአእምሮ ንብረት ባለቤትነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ጨምሮ ስታርትአፖች ለሚሰሯቸው ሥራዎች የሚያገኟቸውን ሀብቶች መልሰው ለሥራቸው ጥቅም ላይ እንዲያውሉ ማድረግን የሚጨምር እና የመሥሪያ የመሸጫ የሚባሉ ቦታዎችን ችግር የሚፈታ መሆኑን አብራርተዋል። በዚህም መንግሥት ትልቅ ውሳኔ



ወይዘሮ ሙፈሪያት ካሚል

ማሳለፉን አስረድተዋል።

ወይዘሮ ሙፈሪያት፤ እንደሚሉትም ‹‹በሥራ ዕድል ፈጠራው አንዱ ትልቁ ነገር ወይንም ጉልበት ሃሳብ ነው። የሥራ ሃሳብ ፈጠራን ያበረታታል። ፈጠራ አለ ማለት ደግሞ ያልተቋረጠ እድገት አለ ማለት ነው። ያልተቋረጠ እድገት አለ ማለት ደግሞ ተወዳዳሪ የሆነ ኢኮኖሚ ይፈጠራል። የኢኮኖሚው ተወዳዳሪነት ደግሞ በዜጎች ሕይወት ውስጥ ትርጉም ያለው ያደርገዋል። ጥራት ያለው ተጠቃሚነትን ማረጋገጥና የሥራ እድል እንዲያገኙ ያልተቋረጠ ገቢ እንዲያገኙ ማድረግን ሁሉ ያካትታል። ሂደቱ ያልተቋረጠ አዳዲስ ፈጠራ ላይ የተመሠረተ የሥራ ሃሳብም ይፈጠራል›› ሲሉ አብራርተዋል።

እንደ ወይዘሮ ሙፈሪያት ማብራሪያ፤ አሁን ላይ የሥራ ዕድል መፍጠሪያ መንገድ የተለየ ሃሳብ እንዲይዝ ተደርጓል። አሁን ያለው አቅጣጫ ድጋፍ ለሚሹ ወገኖች የሥራ ዕድል መፍጠር ሳይሆን፣ ሀብት ሊያመነጭ የሚችል የሥራ ዕድል እንደሚፈጠር ነው። ኢትዮጵያ ወደ ሀብት ሊቀየር የሚችል እምቅ የሆነ ሀብት ወይንም ፀጋዎች አሏት። ከሕዝቧ 70 በመቶ የሚሆነው በወጣትነት እድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ በመሆኑ የሚሠራ የሰው ኃይሏም ከፍተኛ ነው። እነዚህን ዕድሎችና አቅሞች ለሀገር ሀብት በሚፈጥር ሁኔታ መጠቀም ይገባል። ሀብት መፍጠር ሲባል ደግሞ የማይቋረጥ፣ ታይቶ የማይጠፋ፣ ዘላቂነት ያለው የሀብት ፈጠራ ሥርዓት እንዲኖረው ተደርጎ ነው የተቀረጸው።

የሥራ ዕድል ፈጠራ (ኢንተርፕሪነርሺፕ) ባህል በተለመደው አካሄድ ሳይሆን፣ ባልተለመደ መንገድ ችግር መስለው የሚታዩ ጉዳዮችን ኃላፊነት ወስዶ በድፍረት ወደ ዕድል መቀየር ማለት ነው። ይሄን አስተሳሰብ ይዞ ወደ ሥራ መግባት ሳይሞከር ገና በርቀት የሚፈሩና ችግር ይሆናሉ ተብለው አስቀድሞ በስጋት የሚታዩ ነገር ግን በውስጣቸው ወደ ሀብት ሊቀየሩ የሚችሉ ነገሮችና እድልም እንዳላቸው እንድንመለከት የሚያደርግ አዲስ የማያ መነጽር ነው የሚሆነው።

እንደ ወይዘሮ ሙፈሪያት ገለጻ፤ ወጣ ያለ ነገር ለመሥራት የሚሞክሩ ሰዎች አሉ። እንዲህ ያለውን ማበረታታትና ብዙ ሰዎችም እንዲከተሉትና ባህልም ሆኖ እንዲቀጥል ማድረግ ያስፈልጋል። በአካባቢ ላይ ያሉ ፀጋዎችን ለማስተዋል እንዲቻልም የሚያግዝ በመሆኑ ይህንን በመኮትኮት፣ በማሳደግ፣ እንደ ሀገርም ያሉንን እምቅ ሀብቶችንና አቅሞችን አውጥቶ ጥቅም ላይ ማዋል ይጠበቃል። ከእለት ጉርስ ያልተላቀቀ የሥራ ዕድል ሳይሆን፤ የዜጎችን የኑሮ ደረጃ የሚያሻሽል፣ በሀገር የኢኮኖሚ እድገት ላይም ለውጥ ሊያመጣ የሚችል ዘላቂነት ያለው የሥራ እድል መፍጠር ሲቻል በሂደት ሀብት ያመነጫል።

በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ ማብራሪያ የሰጡት ባለሙያዎችና የሥራ ኃላፊዎች፤ ስታርትአፕ ኢንተርፕራይዞችን በተለያየ መንገድ መደገፍ ሀገራዊ ፋይዳው በተለይም ምጣኔያዊ እድገት ላይ የጎላ ሚና ሊኖረው እንደሚችል በማጉላት ነው ሃሳባቸውን ያጠቃለሉት።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# በብድር የስኬት መንገዷን የጠረገችው ሴት



ወይዘሮ ሜላት ደምሰው

**አስመረት ብስራት**

አዲስ አበባ ሽጎሌ ሩፋኤል አካባቢ በ1986 ዓ.ም ነበር የተወለደችው። ገና የስድስት ዓመት ሕፃን እያለች ነበር ወላጅ እናቷን በሞት ያጣችው። የእናት እቅፍን ሳትጠግብ እናቷን ብታጣም አባትም እናትም ሆነው ምንም እንዳይጎድልባት አድርገው አባቷ እንዳሳደጓት ትናገራለች። ለእናትና ለአባቷ ብቸኛ ብርቅ ሴት ልጅ የነበረችው ይህቺ ልጅ በብቸኝነት ማደጓን፤ እሷን ለማሳደግ የተከፈለው የአባቷን ድካም ለመመለስ ስትል ባጠራቀመችው ጥንካሬ ነገን የተሻለ ለማድረግ የምትታትር ውጤታማ ሴት ለመሆን በቃች። አዲስ አበባ ተወልዳ ያደገችው የሃያ ዘጠኝ ዓመቷ ወጣት አሁን ላይ የበርካታ ንብረቶች ባለቤት ሆናለች።

በልጅነቷ እንደ ማንኛውም ልጅ በቀበሌ ቤት ውስጥ በመካከለኛ ኑሮ ያደገች ልጅ ናት። አባቷ የጁቡቲ ሹፌር የነበሩ ሲሆን፤ እሷ ሠራተኛ ተቀጥሮላት በአባቷ ድካምና ፍቅር ማደጓን ታስታውሳለች። አባት ብቸኛ ልጃቸው ልጅነቷን የተሻለ ለማድረግ ሁልጊዜ ጥረት ያደረጉ ሲሆን እድሜዋ ለትምህርት እንደደረሰ በቅድስት ማሪያም ካቶሊክ ትምህርት ቤት ገብታ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ እዛው እንደ ተማረች ታስታውሳለች።

የኢኮኖሚ አቅማቸው አነስ ከሚል፤ በአስተሳሰባቸው የላቁ ቤተሰቦች ውስጥ አድጋ በመውጣቷ የተነሳ ታላቅ ህልምን የሰነቀችውን ወጣት ለስኬት መንገድ ማሳያ ትሆናለች ስንል ለዛሬው በሴቶች ዓምድ እንግዳ ልናደርጋት ወደናል። መልካም ቆይታ።

የዛሬ እንግዳችን ወይዘሮ ሜላት ደምሰው ትባላለች፡፡ በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ዲግሪዋን አግኝታለች። በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ በመደበኛ ፕሮግራም በሲቪል ኢንጂነሪንግ የተመረቀች ሲሆን፤ በማታ የትምህርት መርሀ ግብር ከሼባ ዩኒቨርሲቲ ማኔጅመንት ተምራ ሁለት የመጀመሪያ ዲግሪ በተመሳሳይ ዓመት ይዛ እንደወጣች ትናገራለች።

መጀመሪያ ተማሪ እያለች በቀን ዲግሪ ፕሮግራም በምሽት ደግሞ ማኔጅመንት ተምራ ተመርቃለች። ይህን ጥንካሬ በአፍላው የወጣትነት እድሜ ላይ ልትላበስ የቻለችው ብቸኛ ልጃቸው ተንቀባራ እንድታድግላቸው ሲሉ በበረሃ እየተጓዙ ላሳደጓት አባቷ ስትል እንደሆነ ትናገራለች። ጠንካራ ልጅ ማሳደጋቸውን በተግባር እንዲያዩላት ያሰበችው ወጣትም ትምህርቱን ጠንክራ በመማር ተመረቀች።

እድል መግቢያ በሯን ወለል አድርጋ የከፈተችላት ወጣት እንደተመረቀች አንድ ወር እንኳን ሳትቆይ ነበር ፍያብ ሪል እስቴት ውስጥ ጁኒየር ፕሮጀክት ማናጀር ሆና የተቀጠረችው። ሥራ የጀመረችው ከአራት ዓመታት በፊት እንደሆነ የምትናገርው ወጣት ሜላት በድርጅቱ ተቀጥራ መሥራት በጀመረችበት ወቅት ነበር ድርጅቱ ከሚያገኙት ደመወዝ አስር በመቶ አሚጎስ በተባለ የብድርና ቁጠባ ተቋም እንዲቆጥቡ አስገዳጅ ሁኔታን አስቀምጦ የነበረው።

ሥራ እንደተቀጠረች መጀመሪያ ታገኝ የነበረው ደመወዝ ሁለት ሺ ብር ሲሆን ለአንድ ዓመት ከሠራች በኋላ ነበር ደሞዟ ከፍ ያለው። በወቅቱ ድርጅቱ ከጀማሪነት ተነስቶ ከፍ ሲል በከፍታው ልክ ሠራተኞቹን ለማሳደግ በማሰብ ደመወዙን ወደ 25 ሺ ብር አሳደጉላቸው። የደመወዝ ጭማሪው ትልቅ አቅም የፈጠረላት ወጣት ህልሟ ጥግ ለመድረስ የተለያዩ ሃሳቦችን ማሰብ ጀመረች።

መጀመሪያ ማስተርስ ዲግሪዋን ለመማር በማሰብ ስትቆጥብ የቆየችው ወጣት ለማስተርስ መማሪያ የሚሆን ገንዘብ ሲጠራቀም ያንን ተበድራ ትምህርቷን አጠናቀቀች። ለማስተርስ የሚሆን አርባ ሺ ብር ስትበደር የደሞዟ እኩሌታ የነበረ አንድ ሺ ብር እየተቆረጠ የከፈለች መሆኑን ታስታውሳለች። ከሁለት ሺ ብር ደመወዝ አንድ ሺውን ለማስተርሷ እያጠራቀመች በተጨማሪ ለረዥም ጊዜ የሚቆይ የአምስት መቶ ብር እቁብ እየጣለችም ነበር። እቁቡን ስታጠናቅቅ ብድሯን ዘግታ ጨረሰች።

ከማስትሬት ትምህርቷ በኋላ ደሞዟ ከፍ ሲል በተለያዩ የትርፍ ጊዜ ሥራዎች ገቢ ማግኘት ስትጀምር ቁጠባዋን ከፍ አድርጋ መኪና ለመግዛት አቀደች። እቅድ ጥረት ስኬትን የምታከታትለው ወጣት ምንም ነገር ስታቀድ አይሳካም የሚል እምነት ውስጧ እንደማታስቀምጥ ታስረዳለች።

መኪና የመግዛት ህልሟን ለማሳካት ከቁጠባው በተጨማሪ እቁብ በመግባት ወደ ሶስት መቶ ሺ ብር ታገኛለች። ከዛም ባለቤቷ ሶስት መቶ ሺ ብር ተጨማሪ ገቢ በማድረግ የቁጠባ መጠን ጨምረው ከፍ ያለ ብድር ለማግኘት ቻሉ። የቀደመ በቁጠባ የተጠራቀመው ገንዘብ ላይ በመጨመር ያላትን የቁጠባ ገንዘብ ከፍ በማለቱ ከተቀመጠው ሶስት እጥፍ መበደር ቻለች። በዚህም ለስኬት የሚያንደረድራትን መንገድ በአግባቡ የተረዳችው ይች ወጣት ገንዘቡ ተበድራ የጀቡቲ የጭነት መኪና ገዛች።

በወቅቱ የጁቡቲ መኪና ጥሩ ገቢ የሚያስገኝ የነበረ ሲሆን በወር ከመቶ ሺ ብር በላይ ትርፍ በመያዝ ለብድሩ ስልሳ ሺ ብር እየከፈለች፤ ተጨማሪ ገቢ ስታገኝ ቁጠባው ላይ በመጨመር ገንዘብ ስትይዝ ቆየች። ከዛም የተወሰነ ትርፍ ስታገኝበት መኪናውን ሸጣ ቤት እንዲኖራት ለማድረግ ተጨማሪ ገንዘብ ማጠራቀም ጀመረች።

የነበረባትን ብድር በሙሉ ዘግታ፤ ድጋሚ ቁጠባዋን አሳድጋ መበደር አቅዳ ለመንቀሳቀስ ስትሞክር ባሰበችው ፍጥነት ሊሄድ ባለመቻሉ ለተወሰነ ጊዜ ብድር የመበደር ሀሳቧን ትታ ብድሯን ዘግታ እየቆጠበች ብቻ መቆየትን ምርጫዋ አደረገች። ከዛ ባለቤቷ ይሰራው ከነበረው ገንዘብ ጋር በመደመር በመተጋገዝ ቁጠባ ጀመሩ።

መጀመሪያ ኮንዶሚኒየም ገዝተው በስድስት ወር ሸጠው ያለውን ገንዘብ ጨማምረው የተወሰነውን ገንዘብ ለሪልእስቴት ሼር ሲገቡ በገሚሱ ደግሞ ሁለት መቶ ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ ቤት ገዝተው ማከራየት ጀመሩ። ቤቱ በወር እስከ ሰባ ሺ ብር ስለሚያስገኝ ብድሩን እየከፈለ ሲቆይ ጎን ለጎን የሪልእስቴት ድርሻዋን ከፍ እያደረገች በሜድ የሀብት መጠኗን ማሳደግ ጀመረች።

በአርባ ሺ ብር የተጀመረ ብድር ባጠቃላይ እስካሁን ድረስ አስር ሚሊየን ብር በመውሰድ እየዘጉ መቆየታቸውን ትናገራለች። በትንሹ ደፍራ ታላቅ ባለሀብት ለመሆን መንገድ የጠረገላትን ብድር መጀመሪያ እስክትጀምር ድረስ ለቀናት እንቅልፍ አጥታ እንደነበር ትናገራለች።

"መጀመሪያ ብድር ለመበደር ማሰብ በራሱ ሞት የሚሆንብኝ ዓይነት ሴት ነበርኩ" የምትለው ሜላት "የመጀመሪያዋ ማስተርስ ዲግሪዬን ለማመር ስል የተበደርኳት አርባ ሺ ብር ግን የብድር ዓይነ ጥላዬን ገፎልኛል" ትላለች። በወቅቱ ለመበደር ስታስብ እንቅልፍ አጥታ የነበረ ሲሆን ትምህርቷንም ተምራ ብድሯን መልሳ መኖር እንደሚቻል በመገንዘብ ሃሳቧ ወደፊት ማድረግ ችላለች።

ባለቤቷና አባቷ ለእያንዳንዱ ስኬቷ ቀኝ እጅ እንደነበሩ የምትናገረው ሜላት ባለቤቷ ሰው ተበድሮ የተለያዩ ሥራዎችን መሥራቱ ጥንካሬ እንጂ ውድቀት አለመሆኑን እየነገረ ያበረታት እንደነበር ትናገራለች።

"ሰው መጀመሪያ የሚሠራው ሥራ ያዋጣል ወይም አያዋጣም የሚለውን ጉዳይ ጥናት ማድረግ አለበት፤ ብድር ተበደሬ ምን ሥራ ላይ ባውለው ስኬታማ እሆናለሁ የሚለውን ነገር ማቀድ እጅግ አስፈላጊ ነው። የሚጀመረውም ሥራ ምን ያህል ትርፍ ያስገኛል፤ ትርፉስ ብድሩን እየከፈለ ተጨማሪ ገቢ ሊሆን ይችላል ወይ የሚለውን ግምት ውስጥ ማስገባት ተገቢ ነው" ትላለች። መኪናው በወር ከመቶ ሺ ብር በላይ የሚያስገባ ሲሆን ከዛ ላይ ብድር ስልሳ ሺ ብር እየተከፈለ ትርፍ የነበረው መሆኑ ውጤታማ እንዳደረጋት ትናገራልች።

መጀመሪያ ሰው ከትንሽ ተነስቶ ትልቅ ደረጃ ይደርሳል ሲባል እውነት የማይመስላት እንደነበረ የምትናገረው ሜላት የቅጥር ሥራ ላይ ሆና በምን መልኩ ስኬት ላይ ልትደርስ እንደምትችል ትኩረት አድርጋ ታስብ እንደነበር ታስረዳለች። ሰው በብድር ሥራ ሠርቶ ይለወጣል ሲባል ህልም እየመሰላት የኖረችው ወጣት ህልሟ እውን እንደሆነ በራሷ አይታ ማረጋገጧን ትናገራለች።

ባለቤቷና አባቷ የሚያደርጉላት ድጋፍ ከፍ አድርጎኛል የምትለው ወጣት ከዛም በተጨማሪ በቅጥር ሥራ ላይ መቆየት እርግጠኛ የሆነ ገቢ ይዞ ተጫማሪ ሥራዎችን ለመሥራት የሚያስችል መሆኑን ትናገራለች። በቅጥር ሥራ መቆየት በቢዝነስ ኪሳራ ቢገጥም ምን ይውጠኛል ያለ ገቢ ልቀር ነው ወይ ከሚል ስጋት የሚያፀዳ መሆኑን ታብራራለች።

ከዩኒቨርሲቲ በተመረቀች በዓመቷ ወደ ትዳር ዓለም እንደገባች የምትናገረው ሜላት ትዳር ውስጥ በዚህ ፍጥነት እገባለሁ ብላ ባታስብም ትዳር ውስጥ መግባቷ የበለጠ ብርታት የበለጠ አቅም እንደፈጠረላት ትናገራለች። የትዳር አጋሯ የሥራ ሰው መሆኑ ወድቀትን የማይፈራ ከስህተቱ ተምሮ ለተሻለ ስኬት የሚተጋ መሆኑ ለስኬቷ ጉልበት እንደሆናት ታስረዳለች።

አባቷ በቁጥብነትና በትጋት ሲያሳድጓት ባለቤቷ ደግሞ ሳይሞክሩ ሥራን ከመሸሽ ይልቅ ሞክሮ መሳሳትን፤ ሞክሮ ማየትን እንድትለምድ አድርጎ ነገ የተሻለ ህልም ያላት ባለ ራእይ ሴት እንድትሆን እንዳደረጋት ትናገራለች። "ከስኬታም ሰዎች ጀርባ ጠንካራ ሰዎች መኖራቸው የማይካድ ሀቅ ነው " የምትለው ሜላት የራሷን ድርጅት የምታስተዳድር ሴት የመሆን ህልም የሰነቀች፤ ነገ አንድ በሴት የሚመራ ተቋም እንዲኖራት አልማ ለህልሟ የምትተጋ ሴት መሆኗን ትናገራለች።

አሁን የሁለት ዓመት ሕፃን ልጅ ያላት እናት፤ እንደ አባትም እንደ እናትም ያሳደጋት አባት ልጅ፤ ለባሏ መልካም ሚስት፤ በሥራዋ ጠንካራ ሠራተኛ የሆነች ሴት ሆናለች ወይዘሮ ሜላት ደምሰው። ሜላት "ለዚህ ደረጃ እንድበቃ ላደረገው ለአባቴ፤ በሁሉም ርምጃ ላይ ውጤታማ እንድሆን ከጎኔ ለነበረው ጠንካራው ለባለቤቴ ለፍፁም አብርሃ፤ ሕይወትን በአዲስ ዓይን እንዳይ ያረገችኝን ልጄን ማመስገን እፈልጋለሁ" ትላለች።

ህልም ጥረት የገንዘብ አቅም አንድ ላይ ተደምረው፤ የቤተሰብ ድጋፍ ታክሎበት ውጤታማ ያደረጋትን ሴት ተሞክሮ ስንመለከት በሷ መንገድ ለመጓዝ ድፍረትን እናገኝ ዘንድ ነውና ለመሥራት አቅዳችሁ ህልም እያላችሁ በገንዘብ እጦት የታሰራችሁ ሜላት ገንዘቡ የሚያረፍበት ቦታ ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ ብቻ በቂ ነው፤ ጠንካራ ሥራና የተሳካ እቅድ ለስኬት በር ቁልፉ ነው ትላለች። እኛም ለስኬት ቀን ከሌሊት መጣር እና ያሉትን አማራጮች ሁሉ መጠቀም መልካም መሆኑን ተናግረን የዛሬውን አበቅተናል። ቸር ይግጠመን።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

አስታዋሹን ሲያስታውሱት...የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሠራተኞች ምን ሆኑ...ይህን በተመለከተ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ያወጣው መረጃ ያስታውሰናል:: ሀገራችን ኢትዮጵያ በተሳተፈችበት በኮንጎው የጦርነት ዘመቻ ላይ ስለወታደሩና የገጠማቸው ጉዳይ፤ በጊዜው በአዲስ ዘመን ከሰፈሩ ወቅታዊ ዘገባዎችም ሁለቱን እናስታውሳለን:: ከዚህ ወጣ ስንል ደግሞ "የዝንጀሮ ሥጋ ውዝግብ ፈጠረ " ነገሩ እንዴትስ ይሆን...ማሞ ውድነህም "አበበን አይቼ" ይለናል::

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሠራተኞች በተገኘ የተሻወርቅ ላይ ክስ አቀረቡ

አዲስ አበባ(ኢ.ዜ.አ) የኢትዮጵያ ፕሬስ፤ የጋዜጠኞች ማከፋፈያና ማስታወቂያ ድርጅት አባሎች፤ ክቡር አቶ ተገኘ የተሻወርቅ፤ ምክትል ሥራ አስኪያጅ በነበሩበት ጊዜ በሥራውና በሠራተኞቹ ላይ በደል አድርሰዋል በማለት ለክቡር አቶ አሐዱ ሳቡሬ የማስታወቂያ ሚኒስትር ትናንት አቤቱታ አቀረቡ::

ሠራተኞቹ ትናንት ለማስታወቂያ ሚኒስትሩ ባቀረቡት 29 አንቀጾች በያዘ አቤቱታ ላይ ክቡር አቶ ተገኘ፤ የፕሬስ፤ የጋዜጠኞች ማከፋፈያና ማስታወቂያ ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ በነበሩበት ጊዜ አቋማቸው የማይታወቅ ኤዳና ኢትዮ ማርኬቲንግ የሚባሉ የማስታወቂያ መሰብሰቢያ ድርጅቶች አቋቁመው ለመንግሥቱ ሊገባ የሚገባውን ገንዘብ አላግባብ እንዲባክን አስደርገዋል:: እንዲሁም ከድርጅቱ አባሎች መካከል አንዳንድ ዕድገት የማይገባቸውን ሰዎች ያለደረጃቸው ዕድገት ሲሰጡ፤ አንዳንዶቹን ደግሞ ያላግባብ ከደረጃቸው ዝቅ በማድረግ የሞራል ውድቀት አድርሰውባቸዋል በማለት በዝርዝር አመልክተዋል::

አቶ አሐዱ ሳቡሬ የሠራተኞቹን አቤቱታ ከተቀበሉ በኋላ ጉዳዩን በዝርዝር የሚያጠኑ መሆናቸውን ገልጠውላቸዋል::

**(አዲስ ዘመን ታህሳስ 7 ቀን 1966ዓ.ም)**

**የኢትዮጵያ ወታደሮች በኦሬይንቲል ፀጥታን አስከበሩ**

በኦሬይንቲል ጠቅላይ ግዛት ፓንሰር ቪል ከሚባለው ቀበሌ ውስጥ ሁከት ተነሥቶ 3 የሲቪል ሠራተኞች መሞታቸው ተነገረ:: በዚህ ቀበሌ የሚገኙ ፖሊሶች በሥፍራው ከመድረሳቸው አስቀድሞ የሀገሬው ሰዎች ሆስፒታልንና የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን ለመውረርና ለመዝረፍ አቆብቁበው ይታዩ ነበር::

ነገር ግን በተባበሩት መንግሥታት ስር የሚታዘዙት የኢትዮጵያ ወታደሮች ደርሰው ፀጥታውን ያስከበሩ መሆናቸውን የተባበሩት መንግሥታት ቃል አቀባይ አስታውቋል::

...

የኮንጎ ጠቅላይ ሚኒስተር ሉዊስና የኦሬይንቲል መንግሥት ጠቅላይ ገዥ እስታንሺል በሚገኘው ማረፊያ ቦታ ውስጥ እንዲቆዩ ተደርጓል:: ይህም የሆነበት ምክንያት በኮሎኔል ሞቡቱ ላይ ሴራ ሲያደርጉ በመገኘታቸው መሆኑን እራሳቸው ኮሎኔል ሞቡቱ ለጋዜጠኞች ባደረጉት ንግግር ገልጸዋል::

"ካውሪር ደ አፍሪክ" የተባለው የሚስተር ሉሙምባ ተቃዋሚ ጋዜጣ፤ ሚስተር ሉሙምባን ይደግፉት ከነበሩት 30 የኮንጎ ምክር ቤት አባሎች ውስጥ ሃያ ዘጠኙ የሉሙምባን መሪነት አናውቀውም በማለት ፈጽመዋል ሲል አትቷል::( ሬውተር)

**(አዲስ ዘመን መስከረም 20 ቀን 1953ዓ.ም)**

**የዝና ስም**

በተቀዳሚ ወደ ኮንጎ የተላከው የጠቅል ሻለቃ ወደዚያ ክፍለ ሀገር ከሔደ ጀምሮ በፈጸመው ሥራ ከፍ ያለ የአድናቆትና እንደገና የዝና ስም በየጊዜው ከልዩ ወኪላችን በደረሰን ዕለታዊ ወሬ ተረጋግጧል::

ጸጥታን በማረጋጋትና ሁከት በተነሣበት አገር እየተዘዋወሩ ከተማዎችንና ሰፈሮችን ለመረከብ ተጠንቅቆ በመሥራት ተግቶ በመጠበቅ ለሀገሪቱ ታላቅ ውለታ ውለውለታል::

የኮንጎ ጠቅላይ ሚኒስትር ሚስተር ሉሙምባ የኢትዮጵያን የጦር መኮንኖችና ወታደሮች ታማኝነት በመገንዘብ፤ ወዲያና ወዲህ የሚዘዋወሩት በኢትዮጵያ ኤሮፕላን እንደሆነ የደረሰው ወሬ ጨምሮ አመልክቷል::

ይልቁንም አሁን የሔዱት መኮንኖችና ወታደሮች በዚያ አገር ሲደርሱና አገልግሎታቸውን ሲጀምሩ፤ ኮንጎ በፍጹም ጸጥታ ላይ መገኘቷ አያጠራጥርም::

...

ይህም ወሬ አይደለም በኢትዮጵያ ጀግኖች የሆነና ተደርጎ የታየ ስለሆነ ነጋሪ አያሻም::

...

በመጨረሻ እንደተገኘው ወሬ በኮንጎ ውስጥ የነበረው ሁኔታ እንደቀድሞው ፀጥታው ስለተመለሰ፤ የኮንጎ ሕዝብ የተባበሩትን መንግሥታት ድርጅት ወታደሮች በአክብሮት የተቀበላቸውና በደስታ የተመለከታቸው መሆኑን፤ ከሊኦፖል ድ ቪል የወጣው መግለጫ ያመላክታል::

**(አዲስ ዘመን ጥቅምት 10 ቀን 1953ዓ.ም)**

**የዝንጀሮ ሥጋ ውዝግብ ፈጠረ**

ባለፈው ሳምንት አጋማሽ ላይ በዛየር ተጫዋቾችና በግብፅ ወጥ ቤቶች መካከል አለመግባባት ተፈጥሮ ነበር:: አለመግባባቱ የተፈጠረው የዛየር ቡድን ለምግብ ከአገሩ ይዞት የመጣውን የዝንጀሮ ሥጋ እንዲዘጋጅለት ጠይቆ ወጥ ቤቶቹ አናበስልም ብለው በመቃወማቸው ነው::

በመጨረሻ የዝንጀሮው ሥጋ በተለየ ክፍል እንዲበስልላቸውና ያመጋገባቸው ቦታ ግን በሆቴል ቤቱ ሳይሆን በመኝታ ክፍላቸው እንዲሆን የቀረበውን ሃሳብ የተስማሙበት በመሆናቸው ተፈጥሮ የነበረው አለመግባባት ሊበርድ የቻለ መሆኑን በሬውተር በኩል ከካይሮ የተላለፈው ዜና አስረድቷል::

**ከአዘጋጁ**

በሀገራችን በዱር በገደሉ፤ ቀጭን ከወፍራም፤ ነጭ ከጥቁር፤ ቀይ ከቡላ ቀለም መልክ ያላቸው እጅግ ብዙ ጦጣና ዝንጀሮዎች ይገኛሉ:: እነዚህ የዱር እንስሳት በማሳ ውስጥ የተዘራውን ለቅመው፤ ከጓሮ የተተከለውን ነቅለው፤ ያሸተውንም ሸምጠው የሚበሉ በመሆናቸው ድንጋይ በወንጭፍ ወርውሮ ከማባረርና ቆመጥ ይዞ ከመግደል በቀር በመያዝ ለጥቅም ያዋላቸው የለም::

የዝንጀሮ ሥጋ ለስንቅ እስከመዘጋጀት የደረሰ መሆኑን ለማያውቁት የሚያስገርም ዜና ይሆን ይሆናል:: በሌላ በኩል ደግሞ ይህ የዝንጀሮ ሥጋ ተወዳጅነቱና ተፈላጊነቱ ከወጥ ቤቶች ጋር እስከማጣላት የደረሰ(እጅ የሚያስቆረጥም) ከሆነ አዲስ የሥራ ዓይነት ለመጀመር ዕቅድ ላላቸው፤ ያፋላጊ የማይከፍሉበት የሥራ መስክ ዕድል የሚያገኙበት ሊሆን የሚችል ይመስላል::

**( አዲስ ዘመን መጋቢት 4 ቀን 1966ዓ.ም)**

**አበበን አይቼ**

ጎረቤቴ የሆነ ሰው ድሮ የሚመላለሰው በልዩ ልዩ ተሽከርካሪዎች ነበር:: ከጥቂት ቀናቶች ወዲህ ግን ከቤት ወደ መሥሪያ ቤት ከዚያም ወደፈለገው ቦታ የሚሔደው በሩጫ ሆነ:: ነገሩ ተደናገረኝና አንድ ቀን፤ ምን መጣብኝ ብለህ ትሮጣለህ? አልኩት፤ እርሱም ምንም አልሆንኩም ግን አበበን ካየሁ ወዲህ እኔም እሮጣለሁ ብሎኝ ሸመጠጠ:: (ተፈተለከ)

**ማሞ ውድነህ**

# ዓለም አቀፍ



## እስራኤል በኢራን ላይ የአጸፋ ምላሽ ብትወስድ አሜሪካ ተሳታፊ እንደማትሆን አስታወቀች

ከኢራን የተወነጨፉ ሚሳኤሎችን በማምከን ድጋፍ ስታደርግ የነበረችው አሜሪካ እስራኤል የበቀል እርምጃ ብትወስድ ተሳታፊ እንደማትሆን አስታወቀች።አንድ የፕሬዚዳንት ጆ ባይደን አስተዳደር ከፍተኛ ኃላፊ እስራኤል ልትወስድ በምትችለው የአጸፋ እርምጃ ውስጥ አሜሪካ ተሳትፎ አይኖራትም ብለዋል።

ኢራን ከ300 በላይ ሰው አልባ አውሮፕላኖች እና ሚሳኤሎችን ወደእስራኤል ማስወንጨፏ ይታወሳል።ሙሉ ለሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ ወደ እስራኤል ከተተኮሱት ሚሳኤሎች እና ድሮኖች በእስራኤል፣ በአሜሪካ እና በአጋር ሀገራት ዒላማቸውን ሳይመቱ ተመትተው ወድቀዋል። ከዚህ ከኢራን ጥቃት በኋላ የእስራኤል ቀጣይ እርምጃ ምን ሊሆን እንደሚችል በስፋት ይጠበቃል።

የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ግን እስራኤል ቀጣይ እርምጃዋን በአስተውሎት እንድትወስድ አሳስበዋል። የአሜሪካ ባለስልጣናት ከ300 በላይ የሚሆኑት ሚሳኤሎች እና ድሮኖች ከኢራን፣ ኢራቅ እና ከየመን ወደ እስራኤል መተኮሳቸውን ገልጸው፤ 99 በመቶ የሚሆኑት ጉዳት ሳያደርሱ በእስራኤል እና በወዳጆቿ አማካይነት እንዲከሸፉ መደረጋቸውን ገልጸዋል።

በቀጣናው የነበሩት የአሜሪካ የጦር ጀቶች እና የጦር መርከቦች በርካታ የኢራን ሚሳኤሎችን መትተው ጥለዋል። የሀገሪቱ ባለስልጣናት እንደሚሉት ከ80 በላይ ድሮኖች እና ስድስት ባሊስቲክ ሚሳኤሎች በኢራቅ እና የመን የአየር ክልል ውስጥ በአሜሪካ አማካይነት ተመትተው ወድቀዋል።

ኢራን በዚህ ጥቃቷ 100 ባሊስቲክ ሚሳኤሎችን በተመሳሳይ ጊዜ ወደ እስራኤል አስወንጭፋ ነበር ተብሏል። ከኢራን ጥቃት በኋላ ጠቅላይ ሚኒስትር ኔታኒያሁ እና ፕሬዚዳንት ባይደን ባደረጉት የስልክ ንግግር "ነገሮችን እንዴት ማቀዛቀዝ እንደሚቻል" ተወያይተዋል ተብሏል።

አሜሪካ እስራኤል የአጸፋ ምላሽ ብትሰጥ ተሳታፊ አልሆንም ትበል እንጂ እስራኤል በኢራን ላይ እርምጃ ከመውሰድ መቆጠብ አለባት የሚል ማስጠንቀቂያ ስለመስጠቷ የተባለ ነገር የለም። የብሔራዊ ደኅንነት ቃል አቀባይ ጆን ኪርቢይ አሜሪካ በግልጽ በቀጣናው የተስፋፋ ጦርነት እንዲኖር እንደማትሻ ለእስራኤል አሳውቃለች ብለዋል።

ይሁን እንጂ ኢራን በጥቃቷ የምትቀጥል ከሆነ አሜሪካ እስራኤልን በመከላከል ትቀጥላለች ብለዋል የብሔራዊ ደኅንነት ቃል አቀባዩ። ይህ የኢራን ጥቃት ድንገት የተከሰተ አይደለም። ኢራን ከ12 ቀናት በፊት በሶሪያ ዋና ከተማዋ በሚገኘው ቆንስላ ጽህፈት ቤቷ ላይ በተፈጸመው ጥቃት እስራኤልን ተጠያቂ አድርጋ የአጸፋ እርምጃ እንደምትወስድ ስትዝት ቆይታለች።

ከአሜሪካ በተጨማሪ ይህን የኢራን ጥቃትን በመከላከል ለእስራኤል ድጋፋቸውን ከሰጡ ሀገራት መካከል ዩናይትድ ኪንግደም እና ጆርዳን ይገኙበታል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

## የሶማሊያ የባሕር ላይ ወንበዴዎች የመርከቦች እገታ ቁጥር ጨምሯል



የሶማሊያ የባሕር ላይ ወንበዴዎች አግተን የነበረውን የባንግላዴሽ ባንዲራን የምታውለበልብ መርከብ እና ሠራተኞቿን ለማስለቀቅ 5 ሚሊዮን ዶላር ተቀበልን አሉ። ኤምቪ አብዱላህ የምትባለው ዕቃ ጫኝ መርከብ የድንጋይ ከሰል ጭና ከሞዛምቢክ ወደ ተባበሩት አረብ ኤሜሬቶች እየተጓዘች ሳለች ነበር በሶማሊያ የባሕር ዳርቻ ላይ በባሕር ወንበዴዎች የታገተችው።

መርከቧን አግተው የቆዩት የባሕር ላይ ወንበዴዎቹ መርከቧን እና 23 የመርከቧን ሠራተኞች ለማስለቀቅ 5 ሚሊዮን ዶላር ተቀብለናል ብለዋል። ይሁን እንጂ የመርከቡ ባለቤቶች በድርድር መርከቧ መለቀቋን ቢያምኑም ገንዘቡን ስለመክፈላቸው ያሉት ነገር የለም።

ከቅርብ ወራት ወዲህ በሶማሊያ የባሕር ክልል ውስጥ የመርከቦች እገታ ቁጥር ጭማሪ እያሳየ ነው። በተለይ ካለፈው ኅዳር 2016 ዓ.ም. ጀምሮ በርካታ መርከቦች ታግተዋል። የደኅንነት ተንታኞች እንደሚሉት ከሆነ የባሕር ላይ ውንብድናው የጨመረው በአካባቢው የተለያዩ ሀገራት ጥምረት የባሕር ላይ ቅኝት የሚያደርጉ አካላት ትኩረታቸውን ወደ ቀይ ባሕር ላይ በማድረጋቸው ነው።

የእስራኤል እና የሐማስ ጦርነት መቀስቀስን ተከትሎ በየመን የሚገኙ የሁቲ አማጺያን ወደ እስራኤል የሚጓዙ መርከቦችን ዒላማ ባደረጓቸው ጥቃቶች ምክንያት የቀይ ባሕር የንግድ መርከብ እንቅስቃሴን አውከዋል። ሮይተርስ የዜና ወኪል ሁለት የባሕር ላይ ወንበዴዎች ነግረውኛል ብሎ በሠራው ዘገባ ኤምቪ አብዱላህ መርከብ እና ሠራተኞቿን ለማስለቀቅ 5 ሚሊዮን ዶላር ገንዘብ ተከፍሏል።

"የተቀበልነው ገንዘብ ትክክለኛ መሆኑን ካረጋገጥን በኋላ ገንዘቡን ተከፋፍለን ለቀናል" በማለት አብዲራሺድ ዩሱፍ የተባለ የባሕር ላይ ወንበዴ ለሮይተርስ ተናግሯል። የመርከቧ ባለቤት የሆነው ኬኤስአርኤም ግሩፕ መርከቧ እና ሠራተኞቿን በድርድር አስለቅቄያለሁ ብሏል።

አጃንስ ፍራንስ ፕሬስ የተባለው የዜና ወኪል ደግሞ ሚዛኑል ኢስላም የተባሉ የመርከቧን ባለቤት ድርጅት ባልደረባ ጠቅሶ ባወጣው ዘገባ ነጻ የወጣችው መርከብ በሁለት የጦር መርከቦች ታጅባ ጉዞዋን ወደ የተባበሩት አረብ ኤሜሬቶች አድርጋለች ብሏል። ሚዛኑል ኢስላም "ከባሕር ላይ ወንበዴዎች ጋር ከስምምነት ደርሰናል። ስለተባለው ገንዘብ ምንም ማለት አልችልም። በአሁኑ ወቅት መርከቧም ሆነች የሁሉም ሠራተኞች ደኅንነት የተጠበቀ ነው" ሲሉ ለኤኤፍፒ ተናግረዋል።

እንደ የዓለም ባንክ ግምት ከሆነ እአአ በ2005 እና 2012 መካከል በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ የባሕር ላይ ወንበዴዎች መርከቦችን እና የመርከብ ሠራተኞችን አግተው ከ339 እስከ 413 ሚሊዮን ዶላር የማስለቀቂያ ገንዘብ መጠየቃቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

## የጨረታ ማስታወቂያ
## የጨረታ ቁጥር ም-04 2015/16

የኦሮሚያ ምርጥ ዘር ኢንተርፕራይዝ በስሩ ከሚያስተዳድራቸው እርሻዎች በተለያዩ የምርት ዘመን ያመረተውን የተለያዩ ምርቶች፣ የተለያዩ የቅባት እህሎች እና ብጣሪዎች (የተለያየ ደረጃ ያላቸውን) እንዲሁም ያገለገሉ ፒፒ ባግ (መቋጠሪያ) በጨረታ አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል፡፡

ስለሆነም ተጫራቾች የጨረታውን ሰነድ ከድርጅቱ ጽ/ቤት አሰላ፣ ባሌ ሮቤ፣ ነቀምቴ እና አዲስ አበባ ጎተራ ተሻለ ጋራዥ ባለኬር ህንጻ ቢሮ ቁጥር 403 የማይመለስ ብር 200.00 (ሁለት መቶ ብር ብቻ) በመግዛት በጨረታ መሳተፍ ይችላሉ፡፡ የጨረታ ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ15 ተከታታይ ቀናት አየር ላይ ይውላል፡፡ በ16ኛ የሥራ ቀን ከቀኑ 7፡30 ሰዓት ተዘግቶ በዚያው ዕለት ከቀኑ በ8፡00 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በድርጅቱ መ/ቤት አሰላ፣ ባሌ ሮቤ፣ ምዕራብ ቅርንጫፍ (ነቀምቴ) እና በዋናው መ/ቤት አዲስ አበባ ይከፈታል፡፡

ኢንተርፕራይዙ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር 022-331-39-00/ 29-47 አሰላ ወይም 011-467-38-62 አዲስ አበባ ወይም 022-244-00-11/ 85 ባሌ ሮቤ ወይም 057-660-37-97 ነቀምቴ ደውለው መጠየቅ ይችላሉ፡፡

**ኦሮሚያ ምርጥ ዘር ኢንተርፕራይዝ**

## የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ በልደታ ክ/ከተማ በ07 ወረዳ በ052/1 የቤት ቁጥር በ0014002667 የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ለሚታወቀው ጽዮን ታደለ ደቻሳ ንግድ ድርጅት በግብር/ ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት ከልደታ ክ/ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ከምጠቀምባቸው ደረሰኞች ውስጥ ከቁጥር 0001-0100፣ 0151-0200፣ 0301-0350 ያለው የተሰራበት (ቲኦቲ) የእጅ በእጅ የሽያጭ ደረሰኝ እና ከቁጥር 0001-0100 ያለው የተሰራበት የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ እና ከቁጥር 0001-0100 ያለው የዱቤ ደረሰኝ ስለጠፋብኝ በማናቸውም አካል እጅ ውስጥ ገብተው ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፉ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ይሁንና ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩበት ለልደታ ክ/ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ወይም በአቅራቢያ ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም ጽዮን ታደለ ደቻሳ**

## የጨረታ ማስታወቂያ
## የጨረታ ቁጥር 001/2016 ዓ.ም

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት በምስራቅ ጉራጌ ዞን ጤና መምሪያ የቡታጅራ አጠቃላይ ሆስፒታል አገልግሎት የሚውሉ

*ሎት አንድ የፅዳት እቃዎች፣ የደንብ ልብስ፣ የኤሌክትሮኒክ እቃዎች፣ የህንፃ መሳሪያዎችና የውሃ እቃዎች

*ሎት ሁለት x-ray Mashin Ditecter

*ሎት ሶስት የላብራቶሪ ሪኤጀንት በዚህ መሰረት

1ኛ የታደሰ የንግድ ፈቃድ፣ የግብር ከፋይ መሌ ቁጥር (TIN NUMBER) ያላቸውና የቫት ተመዝጋቢ የሆኑ እንዲሁም የአቅራቢነት የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ።

2ኛ የጨረታ ማስከበሪያ ብር 10,000 (አስር ሺህ) በባንክ በተረጋገጠ የክፍያ ትዕዛዝ (CPO) ለቡታጅራ አጠቃላይ ሆስፒታል ብለው ማሰራት አለባቸው ወይም ጥሬ ገንዘብ በእያንዳንዱ ሎት ማስያዝ አለባቸው።

3ኛ ተጫራቾች በጨረታው ለመሳተፍ በተራ ቁጥር 1 የተዘረዘረሩትን እና ሌሎች የሚመለከታቸው ማስረጃዎች ፎቶ ኮፒ ከመጫረቻ ሰነዶቻቸው ጋር አያየዘው ማቅረብ አለባቸው።

4ኛ ማንኛውም ተጫራች የጨረታ ሰነድ በአንድ ሎት አንድ ወጥ በሆኑ ሁለት ፖስታዎች ኦርጂናል እና ኮፒ በመለየት በጥንቃቄ በሰም በታሸገ ፖስታ ቡታጅራ አጠቃላይ ሆስፒታል ግዥ ፋይናንስ ንብረት በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ዘወትር በስራ ሰዓት ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ባሉት 10 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ ይችላሉ።

5ኛ የጨረታው ሳጥን የሚታሸገው በ10ኛው ቀን 8:00 ሰዓት ሲሆን በዛው ቀን በ8:30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በቡታጅራ አጠቃላይ ሆስፒታል አጠቃላይ ግ/ፋ/ን/አስ/ደ/ስ ሂደት ቁጥር 55 በይፋ ይከፈታል።

6ኛ የጨረታው ሳጥኑ የሚታሸግበትም ሆነ የሚከፈትበት ቀን ቅዳሜ እና እሁድ እንዲሁም የበዓል ቀን ከሆነ ጨረታው የሚከፈተው በሚቀጥለው የስራ ቀን ከላይ በተጠቀሰው ሰዓት ይሆናል።

7ኛ ተጫራቾች የጨረታ ሰነድ የማይመለስ አንድ ሎት ብር 100 (አንድ መቶ) በመክፈል ቡታጅራ አጠቃላይ ሆስፒታል ግ/ፋ/ን/አስ/ደ/ስራ ሂደት ቢሮ ቁጥር 55 ዳይሬክቶሬት የጨረታ ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ10 (አስር) ቀናት ውስጥ ቀርበው መግዛት ይችላሉ።

8ኛ የሚገዙ ዕቃዎች አይነትና ዝርዝር መግለጫ ከጨረታ ሰነዱ ላይ ማግኘት ይቻላል።

9ኛ ተጫራቾች ያሸነፉትን ዕቃ በሙሉ በራሳቸው ወጪ ቡታጅራ አጠቃላይ ሆስፒታል ድረስ በማምጣት ማስረከብ አለባቸው።

10ኛ ሆ/ሉ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

**ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር 0461151172 ወይም 0461150098 መደወል ይቻላል።**

**በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት የምስራቅ ጉራጌ ዞን ጤና መምሪያ ቡታጅራ አጠቃላይ ሆስፒታል**

## Invitation for Bids

**NATIONAL COMPETITIVE BIDDING (NCB)**

FOR THE CONSTRUCTION of coble stone site work kotobe garage

**Procurement Reference Number:- EEU/S&D/NCB/0020/2016**

| no | ITEMS | Bid Security Amount | Bid Opening And Closing Date Respectively | |
|---|---|---|---|---|
| | | | Bid Clothing Date & Time | Bid Opening Date & Time |
| 1 | For Construction of coble stone and open channel at o kotobe garage | 70,000 (seventy thousand Birr Only) | May 08, 2024 G.C at 8:00 P.M (local time) afternoon | May 08, 2024 G.C at 8:30 P.M (local time) afternoon |

**IFB title**:- Construction of coble stone and open channel at o kotobe garage.

1. The Ethiopian Electric utility invites sealed bids from eligible Bidders that have GC-(5) five, (6) six and (7) seven only general Construction Licenses valid for the current Ethiopian Fiscal Year, (EFY, 2016), Trade License valid for the current Ethiopian Fiscal Year (EFY, 2016), VAT Registration Certificate, TIN Certificate, valid Tax Clearance Certificate and with Registration in the Suppliers List of Public Procurement and Property Administration Agency (PPA).
2. Bidding will be conducted in accordance with the OPEN Bid Tendering Procedures contained in the Public Procurement Proclamation of the Federal Government of Ethiopia.
3. Interested eligible bidders may obtain further information and clarification in the following address Piassa, Degoule square Electric Building 2nd floor office no 204 Tel: 011-156-01-48.
4. A complete set of Bidding Documents may be purchased by interested eligible bidders from the above address and upon payment of a non-refundable fee of ETB 300.00 (three hundred Birr) from the first date of this announcement on the newspaper. The method of payment for purchasing the bid document will be by paying the above amount on Ethiopian Electric Utility (EEU) Account no 1000068699332 held at Commercial Bank of Ethiopia.
5. Bid proposals should be submitted to EEU Head office, Staff & Division Procurement Office2nd Floor office no 204, before May 08, 2024 at 8:00 P.M (local time). Late bids shall be rejected and will be returned unopened to the Bidder.
6. All bids must be accompanied by Bid Security, as specified above in the table. The Bid Security shall be in the form of CPO or an Unconditional Bank Guarantee in the name of« **ETHIOPIAN ELECTRIC UTILITY**>>.
7. Bids will be closed and opened in the above date & time in the presence of the bidders or their representatives.
8. The Ethiopian Electric utility reserves the right to accept or reject any or all bids.

**Ethiopian Electric Utility (EEU)**

## ግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ
## የጨረታ ቁጥር:- 02/2016


በአብክመ ደቡብ ወሎ ዞን የወረኢሉ ከተማ አስ/ር ክ/ጽ/ቤት ለጀመረው G+4 ህንጻ የጣራ ስራ ለማሰራት ይፈልጋል፡፡ በዚህም መሰረት የግንባታ ደረጃቸው ጂ.ሲ/ቢ.ሲ 6 እና ከዚያ በላይ የሆኑ የሚከተለውን መስፈርት የሚያሟሉ ተጫራቾችን እንዲጫረቱ ይጋብዛል፡፡

1. በዘመኑ የታደሰ ህጋዊ ንግድ ፈቃድ ያላቸው፤
2 የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN NO/ ያላቸው፤
3. የተጨማሪ እሴት ታክስ /ቫት/ ተጠቃሚ የሆኑ፤
4. የገቢዎች ክሊራንስ እስከ 3 ወር የከፈለበትን መረጃ ማቅረብ የሚችሉ፤
5. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ብር 2 % በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ፣ ቼክ፣ በክ/አስ/ገ/ጽ/ቤት በካሽ በማስያዝ ከሰነዱ ጋር በማያያዝ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
6 አጠራጣሪ መረጃዎች ቀርበዋል ተብሎ ሲታመንበት ኦሪጅናል መረጃዎችን ማቅረብ የሚችሉ፡፡
7. ጨረታው በሚከፈትበት ዕለት ኦሪጂናል የብቃት ማረጋገጫ፣ የንግድ ፈቃድ፣ የምዝገባ ምስክር ወረቀት፣ የቫት ተመዝጋቢ ሰርተፊኬት፣ የቲን ተመዝጋቢ ሰርተፊኬት መረጃዎችን ይዘው የሚገኙ፡፡
8. የሚፈለገውን የስራ ዝርዝር ከሰነዱ ማግኘት ይችላሉ፡፡
9. ተጫራቾች ከአሁን ቀደም በያዟቸው ፕሮጀክት ላይ ማጓተት እና ማጉላላት በመፍጠራቸው ማስጠንቀቂያ /ቅጣት/ ያልተላለፈባቸው ለመሆኑ መረጃ ከአሰሪው መ/ቤትም ሆነ ከከተማ መሰረተ ልማት መምሪያ /ቢሮ/ መረጃ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
10. የዋጋ ማቅረቢያውን ሰነድ (Financial document) በከ/አስ/ገ/ጽ/ቤት ቢሮ ቁጥር 3 በመገኘት ማስታወቂያው አየር ላይ ከዋለበት ዕለት ጀምሮ ባሉት 21 ቀናት ውስጥ በስራ ሰዓት የተቀመጠውን የገዥ አድራሻ እና የስራ ሁኔታ በመሙላት ብር 500 /አምስት መቶ ብር/ በመክፈል መግዛት ይችላሉ፡፡
11. ማንኛውም ተጫራች በጨረታው ለመሳተፍ ከላይ የተገለጹትን በማሟላት የጨረታ ሃሳባቸውን በአንድ ፖስታ ውስጥ ሁለት ፖስታ በማድረግ ኦሪጅናል፣ ኮፒ በማለት ወይም በሁለት ፖስታ ዋና እና ቅጅ በማለት በተለያየ ፖስታ በጥንቃቄ በማሸግ በከተማ አስተዳደሩ ቢሮ ቁጥር 4 በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ማስታወቂያው እየር ላይ ከዋለበት ዕለት ጀምሮ ባሉት 21 ቀናት ውስጥ በስራ ሰዓት እየተገኙ ማስገባት ይችላሉ፡፡
12. ጨረታው ማስታወቂያው አየር ላይ ከዋለበት ዕለት ጀምሮ በሚውለው 22ኛ ቀን ከጠዋቱ 3:30 ታሽጎ 4፡30 ሰዓት ይከፈታል፡፡
13. በጨረታ ሰነዱም ሆነ በፖስታዎቹ ላይ የድርጅቱ ፊርማ እና ማህተም መኖር አለበት፡፡
14. ምንም አይነት ስርዝ ከጨረታ ውጭ ያደርጋል፡፡
15. አሸናፊ ተቋራጭ አሸናፊነቱ ከተገለጸበት እለት ጀምሮ ካሉት 5 የስራ ቀናት በኋላ ባሉት 5 ተከታታይ ቀናት ውስጥ የመልካም አፈጻጸም ዋስትና ከባንክ /ኢንሹራንስ/ በማስያዝ የስራ መርሃግብር፣ የሰው ሃይል አጠቃቀም የሚያሳይ መርሃ ግብር በማቅረብ ከአሰሪ መ/ቤቱ ጋር ውል መውሰድ ይጠበቅባቸዋል፡፡
16. ውክልና በተመለከተ አቻ እና ከዚያ በላይ ካልሆነ በስተቀር ተጫራቾች ስራውን መስራት የማይችሉ ሲሆን ወኪሎች በውክልናቸው ላይ ስራውን መስራት እንደሚችሉ መጠቀስ የለበትም፡፡

**ማሳሰቢያ**፡- መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
-የጨረታ መክፈቻ ዕለት የስራ ቀን ካልሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን ይከፈታል፡፡

**በአብክመ ደቡብ ወሎ ዞን ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር መምሪያ**
**የወረኢሉ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት**

# ስፖርት





# አሸቴ በከሪ የሮተርዳም ማራቶንን አሸነፈች

**ቦጋለ አበበ**

የዓለም አትሌቲክስ የወርቅ ደረጃ ከሰጣቸው ታላላቅ የማራቶን ውድድሮች አንዱ የሆነው የሮተርዳም ማራቶን ከትናንት በስቲያ በኔዘርላንዳ ከተማ ተካሂዷል:: በሴቶች መካከል የተካሄደውን የ42 ኪሎ ሜትር ፉክክርም ኢትዮጵያዊቷ ኮከብ አትሌት አሸቴ በከሪ ቀዳሚ በመሆን አጠናቃለች::

ከውድድሩ የመጀመሪያ ኪሎ ሜትሮች አንስቶ ከሌሎች ኢትዮጵያውያንና ኬንያውያን አትሌቶች ጋር ብርቱ ፉክክር ያደረገችው አትሌት አሸቴ፣ ሃያ አምስት ኪሎ ሜትሮችን 1፡21፡23 በሆነ ሰዓት ከተፎካካሪዎቿ ጋር ካገባደደች በኋላ በአስደናቂ ፍጥነት ጥላቸው ሄዳለች:: ሰላሳኛው ኪሎ ሜትር ላይም ከተፎካካሪዎቿ ጋር ያላትን ልዩነት በስምንት ሰከንድ ጨምራ በጊዜ አሸናፊ እንደምትሆን አሳይታለች::

በመጨረሻም የ35 ዓመቷ ኢትዮጵያዊት በ2:19:30 ሰዓት በድንቅ አጨራረስ የ2024 የሮተርዳም ማራቶን አሸናፊ ለመሆን በቅታለች:: በ2018 ቫሌንሲያ እና በ2019 በርሊን ማራቶንን ያሸነፈችው አሸቴ በ2019 ይህንኑ የሮተርዳም ማራቶን 2:22:55 ሰዓት በማስመዝገብ ማሸነፍ እንደቻለች ይታወሳል:: ዘንድሮ በኔዘርላንዳ ከተማ ለሁለተኛ ጊዜ ስታሸንፍ ያስመዘገበችው ሰዓትም ከቀድሞው ከ3 ደቂቃ በላይ የተሻለ ሆኖ ተመዝግቧል::

በውድድሩ ጠንካራ ተፎካካሪነታቸውን ያሳዩት ኬንያውያኑ አትሌቶች ቪዮላ ኪቢዮት በ2:20:57 ሁለተኛ እና ሳሊ ቼፕዬጎን ካፕቲች በ2:22:46 ሶስተኛ ሆነው ውድድራቸውን አጠናቀዋል።




**አትሌት አሸቴ በከሪ ለሁለተኛ ጊዜ የሮተርዳም ማራቶን አሸናፊ መሆን ችላለች፤**

በወንዶች መካከል የተካሄደውን ውድድር ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ለአሸናፊነት ጠንካራ ፉክክር ቢያደርጉም ቀዳሚውን ደረጃ ይዘው ማጠናቀቅ ሳይችሉ ቀርተዋል::

ኔዘርላንዳዊው የኦሊምፒክ ማራቶን የብር ሜዳሊያ አሸናፊ አትሌት አብዲ ነገዬ በሀገሩ የተካሄደውን ውድድር በድንቅ ብቃት ለሁለተኛ ጊዜ ማሸነፍ ችሏል:: ለድል የበቃበትን 2፡04፡50 ሰዓት ሲያስመዘግብም 2022 ላይ አሸናፊ ከነበረበት 2:04:56 ሰዓት በአስራ አንድ ሰከንድ የተሻለ ሆኗል:: ይህም በራሱ ተይዞ የነበረውን የኔዘርላንድስ ማራቶን ክብረወሰን ያሻሻለበት ነው::

ውድድሩን ቀዳሚ ሆኖ የማጠናቀቅ ትልቅ እድል የነበረው ኢትዮጵያዊው አትሌት አምደወርቅ ዋለልኝ በ2:04:50 በሆነ ሰአት ሁለተኛ ሆኖ አጠናቋል። እስከ መጨረሻዎቹ ጥቂት መቶ ሜትሮች ድረስ ውድድሩን ሲመራ የነበረው አምደወርቅ በትውልደ ሶማሌያዊው የኔዘርላንድ አትሌት አብዲ ነገዬ የተቀደመውም በአምስት ሰከንዶች ብቻ ነው:: ሌላኛው ኢትዮጵያዊው አትሌት ብርሀኑ ለገሰ ውድድሩን በ2:05:16 በሆነ ሰዓት ሦስተኛ ሆኖ አጠናቋል።

ከውድድሩ መጀመር አስቀድሞ ባለፈው የካቲት ወር በደረሰ የመኪና አደጋ ህይወቱን በአሳዛኝ ሁኔታ ላጣውና ይህንን ማራቶን ለመሮጥ አስቀድሞ ወጥኖ ለነበረው የዓለም የማራቶን ክብረወሰን ባለቤቱ ኬንያዊ አትሌት ኬልቪን ኪፕቱም የአንድ ደቂቃ የህሊና ፀሎት ተደርጓል። በርካታ አትሌቶችም አትሌቱን ለማሰብ ጥቁር ጨርቅ ክንዳቸው ላይ አስረው ውድድራቸውን አድርገዋል::

የማራቶን ባለክብረወሰኑ ኪፕተም በሀገሩ በገጠመው የመኪና አደጋ ሕይወቱን ባያጣ በዚህ የሮተርዳም ማራቶን አርባ ሁለት ኪሎ ሜትሩን በዓለም አትሌቲክስ እውቅና የተሰጠው ከሁለት ሰዓት በታች በማጠናቀቅ በታሪክ የመጀመሪያው አትሌት የመሆን ፍላጎት ነበረው::

የሮተርዳም ማራቶን ታሪካዊው ኢትዮጵያዊ አትሌት በላይነህ ዲንሳሞ የዓለም ክብረወሰን ያስመዘገበበት እንደነበር ይታወሳል:: በላይነህ በ1988 የሮተርዳም ማራቶን ነበር ርቀቱን 2፡06፡50 በማጠናቀቅ በወቅቱ አዲስ የዓለም የማራቶን ክብረወሰን ያስመዘገበው:: በላይነህ ይህን ውድድር እኤአ 1987፣1988፣1989፣1996 አራት ጊዜ በማሸነፍ ብቸኛ ታሪክ ያለው አትሌት ሲሆን፤ ከእሱ በኋላ በወንዶች ሮተርዳም ማራቶን የዓለም ክብረወሰን ያስመዘገበ አልተገኘም:: የውድድሩና የቦታው ክብረወሰን ግን 2021 ላይ በአብዲ በሽር 2፡03፡36 የተመዘገበ ነው:: በሴቶች የቦታው ክብረወሰን ደግሞ በለንደን ኦሊምፒክ የማራቶን ባለድሏ ኢትዮጵያዊት አትሌት ቲኪ ገላና 2012 ላይ በ2፡18፡58 ሰዓት እንደተመዘገበ ይታወሳል::

## አዲስ አበባ አስተዳደር

በከሳሽ አቶ አካለወልድ ባንቲርጉ እና በተከሳሽ ሄኖክ ወርቁ መካከል ባለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ በቀን 11/08/2016ዓ.ም በ4፡30 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ 4ኛ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡ በቀጠሮ ቀን ባይቀርቡ በሌሉበት ፍርድ እንዲሰጥ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

በከሳሽ ሰንሰለት የምግብ ማቀነባበሪያ እና በተከሳሽ ቶማስ ገብሬ ማሞ መካከል ስላለው የፍ/ብሄር ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ መከሰሳቸውን አውቀው ክስና ማስረጃዎችን ከሬጅስትራር ጽ/ቤት በመውሰድ መልሳቸውን አዘጋጅተው ለ14/08/2016 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት ሬጅስትራር ቢ.ቁ 113 በኩል መልስዎን ከመዝገቡ ጋር እንዲያያይዙ በተጨማሪም ክስ ለመስማት ለ22/08/2016 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት የተቀጠረ መሆኑን አውቃችሁ በፌ/ከ/ፍ/ቤት 2ኛ ውል ችሎት ፎቅ ቁጥር 2ኛ ቢሮ ቁጥር 201 እንዲትቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡ የማይቀርቡ ከሆነ ጉዳያችሁ በሌላችሁበት ታይቶ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት**

የባለንብረት ስም ነጋሲ ገ/እግዚአብሄር እና አዘዞ ገ/መድህን የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A07667 የተሽከርካሪው አይነት ድርብ አገልግሎት የሻንሲ ቁጥር JT1PDLN4609002456 የሞተር ቁጥር 3L-3114367 ሞዴል HILUX 1N46 የሊብሬ ቁጥር 593846ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር/ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ7/8/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ‘ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪ ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን**
**ንፋስ ስልክ ላፍቶ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም አክመል ሽሄቦ ሃቢብ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-00242 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር JT1HOEP7000107088 ሞዴል EP70L-PHKDSG የሞተር ቁጥር 1E-0113938 የሊብሬ ቁጥር 160964/ 435237/ 531478/017332 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 5/8/2016ዓ.ም አመልክተዋል። የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪ ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን**
**ኮልፌ ቀራኒዮ ቅ/ጽ/ቤት**

## የጨረታ ማስታወቂያ

በአፈጻጸም ከሳሽ---------- አማራ ዲዛይን ቁጥጥር ስራዎች ድርጅት
በአፈጻጸም ተከሳሽ--- ------ ኤምእና ኤ ማንፋክቸሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር
መካከል ስለአለው የአፈጻጸም ክስ ክርክር ጉዳይ በአፈፃፀም ከሳሽ ህንፃ ድርጅት ውስጥ የሚገኘው የእንጨት ስራ ማሽን በመነሻ ዋጋው ብር 12,655,840 /አስራ ሁለት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሀምሳ አምስት ሺ ስምንት መቶ አርባ ብር/ ግንቦት 10 ቀን 2016 ዓ/ም ከጥዋቱ 3፡00 ሰአት እስከ 6፡00 ሰዓት ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ በሐራጅ በግልጽ በጨረታ እንዲሸጥ የአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት ትዕዛዝ በሰጠው መሰረት ንብረቱ በሚገኝበት በባህር ዳር ከተማ በዳግማዊ አፄ ሚኒሊክ ክፍለ ከተማ ፍኖተ ቀበሌ አማራ ዲዛይን ቁጥጥር ስራዎች ድርጅት ህንፃ ውስጥ የሚገኝ በመሆኑ እዚያው በመገኘት መጫረትና መግዛት የሚፈልግ ሁሉ መጫረት የሚችል መሆኑን እየገለጽን፣ የአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሐራጅ ባይ ጨረታውን በበላይነት በመምራት ጨራታው ይካሄዳል፡፡በመሆኑም ጨረታውን መሳተፍ የሚፈልግ ሁሉ ቀርቦ መሳተፍ የሚችል መሆኑን እና አሸናፊው እንደታወቀ ያሸነፈበትን ገንዘብ ከተቻለ ሙሉውን ካልተቻለ ¼ አንድ አራተኛውን ማስያዝ የሚችል መሆኑን የአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት አዟል፡፡

**በአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍታብሔር ዳኝነት አገልግሎት**
**አሰጣጥ ዳይሬክቶሬት**

## የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ በቂርቆስ ክ/ከተማ በ08 ወረዳ በG-04 የቤት ቁጥር በ0003664849 ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) የሚታወቀው ፈለቀች ገብረመድህን ዱቤ ንግድ ድርጅት በግብር /ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት በአዲስ አበባ ከተማ ቁጥር 2 መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ከምጠቀምባቸው ደረሰኞች ውስጥ ከቁጥር 3200-3215 ያለው የተሰራበት እና ከቁጥር 3216-3250 ያለው ያልተሰራበት የተጨማሪ እሴት ታክስ (ቫት) የእጅ በእጅ የሽያጭ ደረሰኝ ስለጠፋብኝ በማናቸውም አካል እጅ ውስጥ ገብተው ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፉ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ይሁንና ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር /ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩበት በአዲስ አበባ ከተማ ቁጥር 2 መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ወይም በአቅራቢያ የሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ።

**የግብር ከፋይ ስም፡ ፈለቀች ገብረመድህን ዱቤ**